My email exchange with a Felasha lady

Getachew Reda
getachre@aol.com
www.ethiopiansemay.blogspot.com
(408) 561-4836

## ከኢትዮጵያዊት ፈላሻ ጋር ያደረግሁት የደብዳቤ ልውውጥ

ይህ ጉዳይ በእኔ እና “አይሁዳዊያን እንጂ ኢትዮጵያዊያን አይደለንም ብለው ከኢትዮጵያ ወደ እስራኤል አገር ከተጋዙ “እምዬ ኢትዮጵያ 9ወር በማህጸንዋ ተሸክማ ካሳደገቻቸው” “የኢትዮጵያ ልጆች” መካካል ከአንዷ ጋር ያደረግኩት የኤልክትሮኒክ ደብዳቤ ልውውጥ ነው።

የደብዳቤው ልውውጥ መንስኤ “አይሁዶች” በቅርቡ ”በፍልስጥኤም” ሕዝብ ማለትም በህፃናት፤አረጋዊያን፤ሴቶች፤እርጉዞች፤ጋዜጠኞችና መሳሪያ ባልታጠቁ ኗሪዎች ላይ የአይሮጵላን ቦምብ በላያቸው ላይ እንደበረዶ በማውረድ “ዘግናኝ” የሆነ የጅምላ ጭፍጨፋ እንዳካኼዱ ታዝበናል። በዚህ ዘግናኝ የመተላለቅ ጦርነት ላይ የፍልስጢኤም ታጋዮችም በተመሳሳይ መልኩ እስራል/ቴልአቪቭ በመሳሰሉ ከተሞች ድረስ በመዝለቅ አቡቶቡስ ላይ በተሳፈሩ ሰላማዊ ሰዎች ላይ “በአጥፍቶ መጥፋት” የሽብር ስልት ቦምብ በማጋየት ሰላማዊ ተሳፋሪዎችን በጅምላ ገድለዋል።ጉዳቱ የደረሰው ማንንም ሳይለይ “እስራሎች እና የውጭ ዜጎችን” ያካተተ ነው።ይህም “የሽብርተኞች ተግባር” መሆኑን ያወገዝኩት ሽብሩ ሲፈጽሙ ከብዙ አመታት ጀምሮ ነው። ምክንያቱም በተመሳሳይ መልኩ ኢትዮጵያ ውስጥም “ሻዕቢያ” ከአስመራ አነጐች እና የራሱ ተዋጊዎችን በመላክ በሰላማዊ ዜጎች ላይ ቦምብ በማጥመድ በሕዝብ ማመላለሻ አውረታሮች...ወዘተ ጥቃት ሲፈጽም አውግዣለሁ። (ይህ ድርጊት ከኢሳያስ መንግሥት እንደተከናወነ መቀበል ያቃታቸው ተቃዋሚዎች ስላሉ ትግርኛ ቋንቋ ለምትረዱ “ከፈረሱ አፍ” እንደሚባለው ነገሩ ሲቀነባባር የዓይን

መረጃው እነሆ Former Eritrean Secret Service Exposes PFDJ (P-1) http://youtu.be/37ePxK09iXo ) ይህ ማለት ግን ከአራዊት ሕሊና መላቀቅ ያቃተው "ሽብርተኛውና ፋሺስቱ የወያነ ትግራይ ቡድን" በሕዝብ ላይ ሽብር አይፈጽምም ማለቴ እንዳልሆነ ብዙ ጊዜ ግልጽ አድርጌዋለሁ።

ስለዚህ የሓማስ ሽብር ስራም ሆነ የአይሁዶቹ የጅምላ የጭፍጨፋ ተግባር ሁለቱም ፋሺስታዊ መሆናቸው ሕሊና ላለው ሰው የሚረዳው ነው።

ወደ አይሁዶቹ እንመለስ እና - በሁሉም በኩል የተካኼደው የመጠፋፋት ጦርነት ለዘመናት የዘለቀ ቢሆንም፤ ከላይ የተጠቀሰው የቅርቡ ሳምንታት የመጠፋፋት ጦርነት ግን አብዛኛዎቹ ትላልቅ የዓለም የዜና አውታሮች "ሓማስ" *ወይንም የፍልስጢኤም ተዋጊዎች ከአገራቸው መሬት "ተምዘግዛጊ ሚሳይል" ወደ እስራል በመተኰስ ያደረጉት ቶከስ የተደጋጋመ ሰፊ የዜና ሽፋን ሲያገኝ፤(ያውም ጥፋተኛ አድርገው በመፈረጅ ዜናው ሲዘገብ)፤ በሌላ በኩል አይሁዶቹ ወደ ፍልስጢኤም መንደር ተዋጊ አይሮጵላኖችን በማሰማራት በሰላማዊ ሕዝብ ላይ አሰቃቂ እልቂት ሲፈጽሙ፤ በጨረፍታ በማሳየት በአንዳንዶቹ የዜና አውታሮችም ጭራሽኑ ሽፋን ሳያገኝ በመቅረቱ፡ እንዲህ ያለ ዘግናኝ እና የናዚ/ፋሺስቶች የጭጨፋ እርምጃ የሚመስል በሕዝብ ላይ ሲፈጸም አይሁዶቹ በራሳቸው ላይ የተፈጸመው የናዚዎች ጭካኔ ከመቼው ረስተውት ተመሳሳይ የአረመኔዎች የግድያ እርምጃ በፍልስጢኤም ሕዝብ ላይ በመፈጸማቸው "ድርጊቱ" ፋሺስታዊ/የናዚዎች ድርጊት እንደሆነ በግል ድረገፄ ላይ አውግዤ ሕዝብ እንዲያውቀው የለጠፍኩትን አብዛኛው ዓለም ያልተመለከተው አሰቃቂ ጭፍጨፋ የተቀረፀ ፊልም በመለጠፌ፤ ይህች አይሁዳዊት ኢትዮጵይያዊት እህቴ የኔን አይሁዶችን ማውገዜን በመኰነን በአይሁድነቷ ወግና ከኔ ጋር አታካራ የሞላበት ደብዳቤ የጻፈቺው እና እኔም ለደብዳቤዋ የሰጠሁትን የተመላለስንበትን ደብዳቤ/ኢመይል እንድታነቡት ስጋብዛችሁ፡- በእኛነታችን ላይ የተዘመተብንን

የተቀነባበረ “ራስን” የማርከስ “ኢትዮጵያን” የማንኳሰስ ባህሪ ምንኛ ሥር ሰድዶ እራሳችንን በማጣት “እራስ ፍለጋ” ቀውስ ገብተን “በተጠነጠነብን ገመድ” ገብተን “ወጥመዱን መበጠስ አቅቶን የገዛ ሰውነታችን “ነክሰን እየጐተትን” የራስ ጉዳተኞች ለመሆን እንዴት እንደበቃን በዚህ የደብዳቤ ልውውጥ ብዙ ቁም ነገሮችን ትታዘባላችሁ።።

የሚከተለው የደብዳቤ ልውውጥ ስትመለከቱ በሕዝባችን ላይ በውጭ ሃይሎች የተፈጸመው ፤የእነሱ ሰለባ ሆነን “ራስን በማጣት ጐዳና እንድንጓዝ” ተቀነባብሮ የተቀየሰልን የጥቃት ዘመቻ ምን ያህል ጥልቀት ይዞ እንዳለ ልብ እንድትሉት ይኼው አንብቡት። ደብዳቤው ላይ በጥቁር ቀለም የተጻፈው ከአስራል የተላከው ደብዳቤ ሲሆን፤ “በቀይ ቀለም” የተጻፈው ደግሞ ከኔ የተሰጠ ምላሽ ነው። የደብዳቤው ለውውጥ ሰፊ እና ሁለት ክፍል ቢኖሮውም፤ አንኳሩን ብቻ አቅርቤዋለሁ። ይኼም ቢሆን በጣም ረዢም በመሆኑ “በትዕግስት” እንድታነቡት-እጋብዛለሁ።

በ01.12.2012
ለአቶ ጌታቸው ረዳ
የኢትዮጵያ ሰማይ ድህረ-ገጽ አዘጋጅ
<u>ባሉበት</u>

ብለሽ ስለጻፍሺሊኝ ደብዳቤ መልሴም እንደሚከተለው ነው።

*<u>ለሃና መከተ፡</u>*
አንቺ ብየ ስጠራሽ ይቅርታ እንደምታደርጊሊኝ ከወዲሁ እጠይቃለሁ። በአይሁዳዊነትሽ በተቀበልሺው እና ባከበርሺው ቋንቋሽ <u>“ሻሎም”</u> ስላልሽኝ እኔም ወላጆቼ በሚናገሩት ኢትዮጵያዊ ቋንቋ ሰላምታ ይድረስሽ <u>“ሰላምታ እንደምን አለሽ”</u> ካለሺበት ጥቁሮች እና ኢትዮጵያዊያን በሚጠሉባት እና በሚዋረዱባት ካለሺበት “ሃገረ

ስራኤል” ‘ሰላም፤ሰላም’ እልሻለሁ።ሰላም ላንቺ ይሁን።

“በመጀመሪያ ለፈጠረኝ የእሥራኤል አምላክ ክብርና ምስጋናዬን ላስቀድም!!”

እኔም በመጀመሪያ ለፈጠረኝ ለኢትዮጵያ አምላክ ክብርና ምስጋናዬን ላስቀድም!!

“ በመቀጠልም ለእርስዎ ካሉበት ቦታ ሰላምታዬን አቀርባለሁ። በእርግጥ ይህን "ኢትዮጵያን ሰማይ" የተባለ ድህረ ገጽ ዛሬ የተመለከትኩት ባጋጣሚ ነው። ይኸውም "ሞሬሽ ወገኔ" የሚለውን ሲቢክ የአማራ ድርጅት በ"ጉገል" ስፈልግ "ኢትዮ-ፓትርዮት" የሚል ድህረ ገጽ አግኝቸ፣ በስተቀኝ በኩል ያሉትን አንዳንድ ጽሁፎች እየከፈትኩ ሳነብ ነው፣"**What is Nazism? See it the Zionist Jew practiced it here on children. Who hate Jesus? Who else?”** የሚል እርእስ ስቦኝ 20 ደቂቃ የፈጀውን
ከአንድ የዓረብ ቻናል የተወሰደውን ፊልም ያየሁት። እሥራኤላውያን በጣም ትእግስተኞች ስለሆን፣ የለጠፉትን ፊልም እስከመጨረሻው በጥሞና ነው የተመለከትኩት። አዲሴ እንኳን ባይሆንም፣
እንደ እናትነቴ ይህን የመሰለ አስከፊ የጦርነት ገጽታ ምንም በማያውቁ ህጻናትና እናቶች ላይ ማየቱ በጣም የሚዘገንን ነው።ሰው በመሆኔና እንደ እናትነቴ በጣም አዝናለሁ!! መላው እሥራኤላውያኑም በጣም ነው የሚያዝን። የጋዛዎቹ እናቶች ግን ከእኛ አንድ ህጻን ሲሞት እልል! እያሉ ከረሜላ ይወረውራሉ።”

ክብርት ሃና፡ እንደ እስራኤልነትሽ ትዕግስት አድርገሽ አሳዛኙ የሰው ልጅ ጭፍጨፋ በዓይንሽ በጥሞና መመልከትሽ አደንቃለሁ። በተለይም “እንደ እናትነቴ ይህን የመሰለ አስከፊ የጦርነት ገጽታ ምንም

በማያውቁ ህጻናትና እናቶች ላይ ማየቱ በጣም የሚዘገንን ነው።ሰው በመሆኔና እንደ እናትነቴ በጣም አዝናለሁ!! ” ስላልሺው የናዚ ጭፍጨፋ ምን ማለት እንደሆነ ከዚያ ርሕራሄ የጎደለው ሆን ተብሎ የተደረገ የከተማ ፍጅት ከናዚ እርምጃ ምንም የሚለየው የህፃናት የግድያ ወንጀል እንደሆነ በጥሞና መመልከቷሽና መላው እስራላዊያንም ማዘናቸው አንድ ነገር ነው። ማዘን ግን በቂ ሊሆን አይችልም። እንዲህ ያለ በሰው ልጅ እየተፈጸመ ያለው መላው ዓለም እና እስራሎችንም ያሳዘነ ጭፍጨፋ በሕፃናት ላይ የፈጸሙ በጫካ ሕሊና የሚመሩ የእስራኤል ባለስልጣኖች የጦርነት ሕግ (ሕግ አስከባሪ ካለ) በመጣሳቸው ምን እርምጃ እንዲወሰድባቸው ጠየቃችሁ? ወይንስ አንቺ እንደምትይው “የጦርነት ገጽታ” በመሆኑ መደረግ የነበረበት ግፍ ነው? ወይንስ አንቺ እንደምትይው <<መላው እሥራኤላውያኑም በጣም ነው የሚያዝን። የጋዛዎቹ እናቶች ግን ከእኛ አንድ ህጻን ሲሞት እልል! እያሉ ከረሜላ ይወረውራሉ>>” እነሱም እልል ስላሉ ህጻናት በቦምብ ሲጋዩ ዜናው ለዓለም መታወቅ የለበትም ነው? አየሽ! የጋዛ እናቶች እንዲህ ያለ ድርጊት በእስራሎች ላይ ሲፈጸም፤ እልል ማለታቸው አስነዋሪ ነው። በእነሱም ይሁን በናንተ መሃል የሰው ልጅ ጭፍጨፋ ሲፈጸም “ሁላችሁም” ማዘን እና ለሰው ልጅ ክብር መስጠት እንጂ “የጦርነት ገጽታ” በመሆኑ ወይንም አንቺ እንደምትይው ለጭፍጨፋው መነሻ ወታደራዊ “የተሳሳተ መረጃ” ስለተላለፈ ድርጊቱ በስሕተት ተፈጽሟል፡ የምትይው “የወንጀል መሸፈኛ” “ሁለታችሁም ወገኖች ከዚህ ሰብአዊ ግፍ ብያንስ የሕሊና ተጠያቂነት ነጻ አያደርጋችሁም። ሁለታችሁንም ወገኖች :”የተሳሳተ መረጃ” “የጦርነት ገጽታ” ወይንም ፍልስጠማዊያን እንደሚያደርጉት “ቦምብ ይዘው ሰላማዊ ሰዎችን በአብቶብስ ተሳፍረው ራሳቸውን ገድለው ሰላመዊንም የሚገድሉ “ሽብርተኞች” ነፃ አውጪዎች ሳይሆኑ “ሽብርተኞች” ናቸው። ስለዚህ በሁለታችሁ ወገኖች ያሉት ጠጅምላ የግድያ ፈጻሚ ክፍሎች/ባለስልጣኖች/ድርጅቶች/ግለሰቦች “ተጠያቂነት እንዲኖራቸው እና ወደ ፍርድ ቀርበው ካልተቀጡ/ከስልጣን ካልተወገዱ” በቃላት ብቻ ማዘን ለፍትሕ የሚረባው የለም። አንቺ የእስራል አምላክ

የምትይውም ሆነ እነሱ “አላህ” የሚሉት “በሁለቱም ወገን እየተደረገ ያለው “ግፍ እና ግድያ” እንደሚቃወመው አንቺም የምታውቂው ይመስለኛል። አንኳን ለፈጣሪ ላንቺም ሳይቀር ጭፍጨፋው “አሳዝኖኛል”። ይህ ግድያ “የናዚዎች ድርጊት ነው” የምለውም ለዚህ ነው”። አንቺን ያሳዘነ ድርጊት “ጭፍጨፋ ነው” ወንጀል ነው ያልኩት። መሸፋፈን አምላክሽ አይወደውም። ግልጽ እንድትሆኚ አበረታታሻለሁ። አምላክን እንጂ ሰውን፤መንግስትን አትፍሪ። መንግስቶች፤ሰዎች ግፍ ሲፈጽሙ “መቃወም ማውገዝ አለብሽ። አምላክ ስትፈሪ “እውነቱን” ይገለጽልሻል። ያኔ የተባረክሽ የሱ ልጅ ትሆኚያለሽ።

**እስከ መጨረሻው በትዕግስት አንብነበው!! በጊዜ <<ማጣት ምክንያት የእንቅልፍ ጊዜየን የተሻማ ጽሁፍ ነውና !!**

03.12.2012

አሁንም በድጋሚ እላለሁ ለእሥራኤል አምላክ ክብር ምሥጋና ይግባው!!

ይህን ሁሉም የኢትዮጵያ ህዝበ ክርስቲያን ከመምኘታው ሲነሳ ወይም ሲተኛ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚለው የተለምዶ አባባልም መሆኑን አውቃለሁ። እያንዳንዱ በፈለገው ማምለክ መብቱ ነው፣ መብትህን አልጋፋውም። >>

ስላለሺው መልስ ይኼው መልሴ የሚከተለው ነው።

04.12.2012 ከጌታቸው ረዳ

ለክብርት ወ/ሮ ሃና መከተ፡ እስኤራል አገር ።

ጥሩ ብለሻል። የእንቅልፍ ጊዜሽን የተሻማ ጽሁፍ ስለ እኔ መልስ የጻፍሺውን በትእግስት አነበዋለሁ። ለዚህ አክብሮት እሰጥሻለሁ። መልካም ብለሻል። ያ የተለምዶ አባባል ነበር። እንዳንቺው ዓይነቱ የዋህ "ተለምዶ" ይለዋል። ሃቁ ግን "ተልመዶ ሳይሆን " ለዘመናት ያንን በሕሊናው ተቀርፆ "የእስራል አምላክ" እንዲል "የአእምሮ አጣባ" ስለተደረገበት ነበር። ዛሬ ያ ልምድ ቀስ በቀስ ማንነቱን እና አምላኩን እያወቀ በሌላ አገር ሳይሆን በገዛ አገሩ አምላክእና መንፈስ የማወደስ ልምድ ተለማምዶታል። መዝሙራችን "የእስራል ልጆች" ተብሎ እንዲለወጥ የተሞከረውን ያህል ዛሬ በጠንካራ ኢትዮጵያዊያን ልጆቿ አሁንም በድጋሜ "የኢትዮጵያ ልጆች ነን" አንጂ "የእስራል ልጆች" አይደለንም ማለት ጀምረናል። ይህ ዘመቻ ነው የኔ ግምባር ቀደም አስተምህሮ። አንዲህ እራሳችንን አውቀን በማንነታችን እንድንኰራ ያደረገን "የኢትዮጵያ አምላክ" በድጋሜ ክብር ምስጋና ይግባው። ይህ ኢትዮጵያዊ መብት ስላከበርሺልኝም አከብርሻለሁ።

<<ኢትዮጵያዊ ነኝ ብለህ ለመኩራራትና ጉራም ለመቸርቸር ሞካከር።>>

ስለምትይው ሰንካላ መልስሽ አስገርሞኛል። አንድ ኢትዮጵያዊ ማንነቱን ጥሎ እራስ ፍለጋ ቀውስ ውስጥ ገብቶ "እስራኤል አንጂ ኢትዮጵያዊ አይደለህም" ተብሎ ሲነገረው "በቂላቂልነት" አዎ "እስራኤላዊ ነኝ አንጂ "ኢትዮጵያዊ ይደለሁም" ብሎ የሚኩራራ የማሰብ ችሎታው ያቆመ "የዋህ እርግብ" እራስን ለውጭ አገር አታላዮች "ከመቸርቸር" ወዲያ የሚታይ "ውርደት" ምን ሊኖር ይችላል? ኢትዮጵያዊነትን የቸረቸረው እኔ ወይስ አንቺው?በምን ሂሳብ? ጣሊያንም፤ወያኔም ሆነ በፈረንጅኛ ዘመን አቆጣጠር የሚቆጥረው የኤርትራው ሻዕቢያም እኮ ኢትዮጵያዊነትን ከሥር-ከሥር እያፈረሱ "ስለ ኢትዮጵያ እንቆረቆራለን፤እናሰለጥናለን" ሲሉን የነበሩ እና አሁንም እያሉን ያሉት። ኢትዮጵያ ስላለ ሁሉም ስለ ኢትዮጵያ የሚቆረቆር ይመስልሻል? ያ ሴራ ነው መበጠር አለበት እያልኩኝ ያለሁኝ። የኤርትራ ስቃይ አማራው እና ኢትዮጵያ ነበረች፡ የሚሉ ውጭ የሚኖሬ ተቃወሚ ነን የሚሉ በኢሳያስ አፈወርቂ

ድግስ/ፌስቲቫል እየተገኙ የኤርትራ ግንጣላ እና የባሕር ወደብ ነጠቃ “ሕጋዊነትና ፍትሕን” የተከተለ አይደለም ስለምንለው
የሻዕቡያ ሴራ እየተቃወምን ላለን ሁሉ “ኤክስትርሚሰት” የሚል ስም በጣም ዘግናኝ ስም እኮ እየለጠፉብን ነው። አሁንም እኮ ደረታቸው ላይ “ኢትዮጵያ” የሚል ከናቲራ ደረታቸው ላይ ለጥፈው ለሕዝብ እያሳዩ ባገራችን  ስም እኮ ነው የ1991 ታላቁ ሴራ ለመድገም አስፍስፈው የሚገኙት። ኢትዮጵያ እያልሽ አይደለ አንቺም ይኼው አማራውን የጠመድሺው! ወይ አንቺ “ኢትዮጵያ” ስምሽ ማመሩ!

<<አንድ ኢትዮጵያዊን ኢትዮጵያዊ ከሚያሰኙት ገፀ ባህርያት ውስጥ፣ ፍጹም የማያውቁትን ሰው መዘንጠል ወግና ባህሉ አይደለም። >>

አንድ የኢትዮጵያዊ ባህሪ ከሚያሰኘው ገጸ ባህሪያት ውስጥ  አንዱ “ሆን ብሎ” እራሱን አጥቶ እንደገና እራስ ፍለጋ  ገብቶ አማራውን ተጠያቂነት የሚያደርግ “በራስ ውዥምብራምነት የሚናወጥ” ሰው ካየን “ውዥምብራሙን-ውዥምብራም“ “ማንነቱን የካደ” ደግሞ “ካሃዲ” “አሾክሷኪውን” ደግሞ አሾክሻኪ” ባንዳውንም ፧ባንዳ፧ የማለት ባህሪ አንቺ አታውቂውም እንጂ “ወይንም እረስተሺው ይሆናል እንጂ” እንዲህ ያለ በማንነት ፍለጋ የሚሰቃይ ግለሰብ “በአንቱታ” አልጠራውም። ራሰን ጥሎ  እንዲህ ዓይነት ቅሌት ገብቶ በራስ ፍላጋ ቀውስ የሚናወጥ በተለይ “ተማርኩ፧ድግሪ አለኝ” ከሚለው የዋዝቀ መስመር ለሚያስተጋባ ድምጽ ከበሬታ የለኝም።

<<እኔ ድህረ ገጽህ በለጠፍከው ፎቶህ ላይ ማንነትህን ግምት ውስጥ በማስገባት ከወዲሁ ዘንጥየ ክብር ሳልሰጥ መጻፍ እችል ነበር። ሆኖም ወግና ባህሉ ለምን ብዬ "አንቱ" በማለት ነበር ጽሁፌን የደመደምኩት። >>

አንቺ አንተ/አንቱ አልሺኝ አላልሺኝ በኔ ላይ ቦታ የለውም። ካንቺ የምፈልገው "አንቱታ" ማንነትን ማክበር ነው፤ጥቁር ሕዝብን ማክበር ነው፤ስደተኛን እንደራስ ማክበር ነው፤ ሰብአዊ መብት ሲጣስ ለፍልስጤማዊያኑንም መጮህ ነው። ለኔ ክብር ማለት አይሁድ ሆንሽ አልሆንሽ ፍልስጠማዊውን ህጻን በዘረኞች ቦምብ ሲደበደብ "የተሳሳተ መረጃ ነው" ወይንም " ፍልስጤሞች እኛኑን በሚሰይል እየተኮሰብን ስለሆነ፤ መንግስታችን አጸፋወን በዚያ ዓይነት አስነዋሪ ጭፍጨፋ ማድረጉ መንግስታዊ ግዴታው ነው" የምትይው በጣም አስነዋሪ መከላከያ አልወደድኩትም ። ያንን ጭፍጨፋ በምንም መልኩ ይፈጸም "የናዚዎች" ባሕሪ መሆኑን ስታወግዢው ያ ላንቺ ከበሬታ እሰጣለሁ። ከዚያ ወዲያ ምትዘላብጂው ነገር ምንም አይጥመኝም።

<<ምሁር ለመምሰል ለዘባረክልኝ ሁሉ ጊዜ ማጥፋት ስለማልፈልግና ለወደፊቱም ምንም ጊዜ ስሌለለኝ፣ ለእንደ አንተ ያለ ሰው ይህ የመጨረሻ መልሴ ይሆናል። >>

ከኔ ጋር የመጨረሻ መልስ ሊሆን ይችላል። የራስ ፍላጋ ስቃይሽ ግን መጨረሻ ሊሆን ከቶ አይችልም። በራስ ቀውስ የሚናወጥ ሕሊና ያንን ማንነቱን ተመልሶ ካላነሳው "መጨረሻ የለውም"።

<<ካንተ ለወደፊቱ የሚላኩትን ላለማየትም ቃል እገባልሃለሁ። ምክንያቱም እሥራኤሎች ካስተማሩን አንዱ፡- ብዙ በመናገር ጊዜን ከማጥፋት ትንሽ ተናግረህ ብዙ የተግባር ሥራ ስራበት ጥሩ ውጤት ታገኛለህ ይላሉ። >>

ላንቺ አዘንኩልሽ። እስራኤሎች አስተማረኝ እያልሽ ያነን "እስራኤል እስራኤል" የሚያስብልሽ "የራስ ቀውስ/ ሲንድሮም" ካስተማሩሽ ይልቅ "አገርሽ ኢትዮጵያ" ያስተማረቿሽን "በራስ የመተማመንን፡

አጥብቀሽ ማስቀደሙን አይበልጥሽም ነበር ወይ? አገርሽ ኢትዮጵያ ያስተማረቺሽን ወደ ጐን እያስወገድሽ “እስራልን” በምሳሌ የምትጠቅሺውን በሽታሽ ምሕረት እንዲያወርድልሽ “ ወደ ኢትዮጵያ አምላክ” ፊትሽን አዙሪ። ኢትዮጵያ ያስተማረቺሽን አንጂ እስራል ያስተማሩሽን “ኢትዮጵያን” የመካድ ማንነትን ደጋግመሽ ስትኩራሪቢኚ “ያቅለሸልሸኛል”። እስራኤሎች አስተማሩኝ ብለሽ የምትመጻደቂበት ባሕሪ ይህንኑ ነው? እስኪ በሌሎች ዘመዶቻችን ምን ጥቃት እየደረሰባቸው እንደሆነ “አስተማሩኝ የምትይውንም “ ትንሽ ላሳይሽ?**Israeli Ethiopian march against racism** [**http://youtu.be/VsaLX61-6P4**](http://youtu.be/VsaLX61-6P4)

<<በመሆኑም ተበታትነው ከነበሩበት ዓለማት እንደገና ተሰባስበው በ-64 ዓመታት ውስጥ እንዴት በቴክኖሎጂ እንደመጠቀች ታሪክ የማይከደው ሃቅ ነው። >>

ወ/ሮ ሃና መከተ፡ እውነትም የዋህ ነሽ። የዚህ ዓለም ጠማማነት የማታውቂ “አርግብ ነሽ፡፡ ለዚህም ነው ላንቺ አዘንኩልሽ የምልሽ” ። የምን ቴክኖሎጂ ነው የምታወሪው? አንዳንቺው ዐይነቱ ቴክኖሎጂ ገባያ ውስጥ አስግበተው “አይሁድ ነህ” ሲሉት “ ኢትዮጵያዊነቱን” ክዶ በሁለተኛ ዜጋ እየታየ “ባርያ፤የኤይድስ ተሸካሚ” እያሉ ከኢትዮጵያ ምድር ሰው እየሸመቱ ወደ ጦርነት ቦታ (ባፈር ዞን) አጥር እንዲሆንላቸው መዳረግ “በቴልኖሎጂ መመንጠቅ” ነው? የቴክኖሎጂ መመንጠቅ የምትይው ሞኝነትሽ “አንዳንቺው ያለው “የዋህ” የቴክኖለጂያቸው ተጠቃሚ አይደለም። ባንቺ መሰል ኢትዮጵያ አይሁዶች እየተፈጸመ ያለው “የቤት መኖሪያ እና የቴክኖሎጂ እገዳ” አታውቂም? ይልቁንስ “ቴክኖሎጂያቸውን” የሰው ልጅ በተለይ ጡቁሩን እንደ ሰው እንዲመለከቱት አንዲረዳቸው “ፈጣሪ” የለገሳቸውን ሕሊና ወደ “ሰብአዊነት ምጥቀት” አንዲጠቀሙበት አንዲረዳቸው ብትታገይ ይሻላል። ያንን ባርነት ተቀብለሽ “ስለ

ቴክኖሎጂአቸው" ብታደንቂ "አሁን ራስሽን አንደገና በኢትዮጵያዊነት ቅኝት አንድትቃኚ እምክርሻለሁ"። ራሱን ጥሎ የጣሉትን እና የሚያንቋሹሹትን "የነጭ ዘረኞች" የማወደሱን "ግብዝ ልምድ" ካስተሳሰብሽ ጣይው። እስራሎች አንዲህ ሲሉ አስተማሩኝ፤ እንዲህ ኰትኩተው አስተማሩኝ;......የምትይው የዋህነትሽን መልክ እንዲኖሮው ይረዳሽ ዘንድ ከላይ የሰጠሁሽኝ ሰነድ "ከቴክኖሎጂ" እድገታቸው ጋር ምንኛ "ወደ ኋላ እንደቀሩ" ከዚህ ወዲያ ምን መረጃ ልስጥሽ? http://youtu.be/VsaLX61-6P4 ቴክኖሎጂያቸው ይህንን ዘረኝነታቸወን ለምን ሊያግደው አልቻለም?

<<በ ር ቀ ት ታ ሪ ክ እ የ ጠረ ቁ ወ ረ ቀ ት ላ ይ መጽሐፍ ላይ ቢለ ከ ለ ክ ለ ሚሰ ቃየ ው የ ኢ ት ዮ ጵ ያ ህ ዝ ብ ጦ ር ና መሳ ሪ ያ ፣ ወሃ ና ዳ ቦ ሆኖ ፣ ከ ራ ብና ከ ጥ ማት አ ስ ታ ግ ሶ ሃ ገ ሩ ን ና እ ሱ ን ሊ ከ ላ ከ ል በ ት አ ይ ች ል ም። >>

እስራሎች የወያኔ እና የደርግ ሰዎችን በገንዘብ እየደለሉ ፈላሻዎችን እንዲያሻግሩላቸው በባርነት እየገዙ ኢትዮጵያዊያንን የሚያንኳስሱ "በቴክኖሎጂ ሰልጥነው" "በሰብአዊ ይዘት ግን የጫካ ሕሊና የሰተሸከሙ የኋሊት የሚራመዱ "የእስራል ባለስልጣኖችም ሆኑ ሌሎች"፡ የሚፍሩት አንድ ነገር ቢኖር "ኢትዮጵያዊያን/አፍሪካዊያን" ታሪካቸውን በመጽሐፍ እየተጻፈ ማንነታቸውን የሳቱ ዜጎችም ካሉ አገራቸው በሚወዱ ጸሐፍቶች በሚጻፉ መጽሐፍቶች እየተረዱ እራሳቸውን አንዳያስተካክሉ የሁሌም ፍራቻቸው ነው። አንዳንቺው ዓይነቱን የዋህ "መጽሐፍ" አትጻፉ "በእንጀራ እና በውሃ ፍለጋ ብቻ አትኩሩ" አንድትሉ የሕሊና አጠባ በማድረግ አንቺኑን የፕሮፓጋንዳቸው ሰለባ አድረገዋል። ሞኝነትሽ ግን አንቺን መሳይ "የዋህ ኢትዮጵያዊት እርግብ" የመጽሐፍ ጠቃሚነት አንዲያንኳሰሱ ቢያስተምሩሽም "እስራሎች ቴክኖሎጂያቸውም ይሁን ታሪካቸው በመጽሐፍ አንዲቀረጽ እና አይሁዶች የራሳቸው ማንነት ታሪክ እንዲያውቁ "ከውሃ አና ከእንጀራ" ቅድሚያ ለመጽሐፍት ነው

የሚሰጡት። ምክንያቱም መጽሐፍ የእድገት፤የማንነትና የታሪክ አፈላላጊ ምንጭ ነው። አንዳንቺው ያለው "በራስ ቀውስ" የገባ "ወደ እንጀራ የሚያንጋጥጥ" ግን ያንን የሆድ ጉዳይ ቅድሚያ ቢሰጥም ፤ እውነተኛ ዜጋ ግን "በመጽሐፍ እየተደገፈ እራሱን እየተከላከለ" እንዲያድግ እና "ጠላቶች/ተንኮሎኞች" እንዳይቦሮቡሩት እና ወደ ሌላ ዓለም እንደባርያ እንዳይሸጡት እውነተኛ አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያን ደራሲያን ከጠላቶችና ከቅጥረኞች ጋር የሕሊና ጦርነት ያካሁዳሉ። የኔ ስራ እና ቀዳሚ ተግባሬ "በኢትዮጵያዊነት የተዘመተበትን" ጦርነት ለማክሸፍ ነው። "መጽሐፍ እየጻፍኩ ያለሁትም" ይህንኑ ጥቃት ለመከላከልና ለማጋለጥ የማደርገው ታሪካዊ ዘመቻ ነው። አንቺንም እዚህ ታሪክ ይጨምራል። ማንነታቸው ከተዘመተባቸው የኔው ዜጎች አንደኛዋ አንቺ ነሽና 'አሁንም የኢትዮጵያ ሕዝብ "ስለ ለሆዱ'ለከርሱ ብቻ እንዲያስብ" የሚወተውቱ ግለሰዎችን/ቡድኖችን'መንግስታቶችን ፊት ለፊት መጋፈጥ የታሪኩ አደራ አለብኝ። እና ወደድሽም ጠላሽም "በኢትዮጵያዊነት የተከፈተው ጦርነት" መጻሕፍቶቼ ግንባር ቀደም ተዋጊዎች ናቸው እና "ኮሎኒያሊስቶች እና ቅጥረኞች" ኢትዮጵያዊያን ዜጎች በየዓለማቱ ተሰድደውም ሆነ ራሳቸውን ሸጠው በሁለተኛ ዜጋ እንዳይታዩ በድል እንዲወጡ "በይሁዶች አገርም ይሁን በፔትሮ ዶላር የሰከሩ ባርያ ፈንጋይ ጥጋበኛ አረመኔ ዓረቦች አገር" እየተሰደዱም ሆነ ዜግነታቸወን እየሸጡ የሚንገላቱ ወገኖቼ ላይ "የሚፈጸምባቸው ጥቃት" እራሳቸውን በክብር እንዲያነሱ እና እንዲከላከሉ ማድረግ የመጽሐፍቶቼ መነሻዎች ናቸውና "ወደድሽም ጠላሺም" መጽሐፍቶቼ "ሕያው ናቸው፤ ለዘላም ይኖራሉ።" መጽሐፍቶቼን የሚጠሉት እና ክብር የሚነሱት ፡እራስ ፍለጋ ገብተው ቀውስ የገቡ፤ ኢትዮጵያዊነትን የሚጠሉ ወይንም "አማራን" እየጠሉ የተቃወሰ ሕሊና ያላቸው ክፍሎች ብቻ ናቸው።

<<ጀግና አገሩንና ህዝቡን ወዳድ ማለት ከህዝቡ ጋር ሆኖ፣ ወገን የሚኖረውን እየኖረ እንደ እነ እስክንድር ነጋ፣ ርዕዮት ዓለሙና እንደነ ተመስገን ደሳለኝ፣ አንዱ ዓለም አራጌ፣ ....ወዘተ እየተጋፈጡ

ሲኖር ነው፣ እንጅ ባህር ማዶ ሆኖ ቢያቅራሩት ትርፉ ማደንቆር ነው። ኢሕአፓ ምንም የማያውቁ ወጣቶችን ለሞትና ለእስር አጋፍጦ ዛሬ ባህር ማዶ የተንደላቀቀ ኑሮውን እንደሚኖረው ማለት ነው የሚሆነው፡>>

ስለታሰሩት ጀግኖች ማወደሲሽ አደንቃለሁ። ስለ ሕዝባቸው ብለው በወያኔ የተገደሉ፤ደብዛቸው የጠፋ የኢሕአፓ ታጋዮች እንደ እነ ፀጋየ ደብተራው፤አበራሽ ወዘተ....የመሳሰሉስ ምነው ረሳሻቸው? ወይንስ ኢሕአፓ፤ ኢሕአፓ ሲል ደርግ ወይንም ወያኔ ከሕሊናሽ የማይፍቅ ጥላቻ እንድታሳድሪ ስላሳደረብሽ ነው? እነሱ ጋር ስትደርሺ ምነው እውቀቱ አጠረብሽ ? ባለ ዲግሪ የተማርኩኝ ነኝ ትያለሽ፤ ማን ከወያኔ ጋር በጥይት ተታኩሶ የተሰዋ፤ደብዛው ጠፋ፤ላገሩ ጠመንጃ ተሸክሞ’ አካለ ጐደሎ ሆኖ፤ ቁር፤ርሃብ ተጋፈጦ የነበር?” የሚለው ጥያቄ ለምን አልጠየቅሺም? “አካላታቸው ጎድሎ፤አሁንም በየአውሮጳ እና እስራል እንዲሁም አሜሪካ አገር በስደት የሚንከራተቱትን ታሪክ ማስታወስ እንዴት አቃተሽ? “የተንደላቀቁ የምትይው “ምቾታቸው” ምቾት ያድርግልሽ ብልሽ “ትቀበይው አለሽ? አገር ጥሎ መሰደድ ኑሮ ነው? መንደላቀቅ ነው? ጥፋት አድረገው ከሆኑ፤ ጥፋቱን ማስታወስ ተገቢ ነው፡ ነገር ግን “ጭራሽኑ” አንደ ጻረ ኢትዮጵያ አድርገሽ ስትመለከቺ ምነው ኢሕአፓዎች መብት እና ገድል ማንኳሰስ መረጥሽ? አማራዎች ናቸው ብለው ያስተማሩሽ እና አማራን የመጥላት አባዜሽ ይሆን እነሱን የመጥላት ዘመቻ ማስተጋባት የመረጥሺው? እዚህ ደብዳቤ ውስጥስ እኔና ኢሕአፓ ለምን ማገናኘት ፈለግሽ? አንቺ “በመንደላቀቃቸው” የምትወቅሺያቸው ኤሕአፓዎች የምታውቂው ነገር እንደሌለ ካነጋጋርሽ ገና “የህጻን ልጅ” እውቀት እንዳለለሽ ያሳያል። መንደላቀቅ የምትይው “ሲባል” ሰምተሽ ነው ወይስ የምርሽ ነው?

አንድ ዜጋ የበቃወን ያህል ታግሎ በቃኝ የማለት መብቱ “ያስወቅሳል”? አንቺ ገና ወጣት ነሽ ወደ እስራኤል የመጣሺው በ1981 ነው። ደርግ

ገርፎኝ ኑዛዜ አልሰጠሁም ብለሻል። የማን አባል ሆነሽ ነው ደርግ አስሮ የገረፈሽ? የኢሕአፓ? በጣም የገረመኝ ግን የጠቀስሺያቸው የምታደነቂያቸው የፖለቲካ እስረኞች መታሰራቸው ወንጀል ነው። ያልገባሽ ነገር ግን "ሰዎች" ብቻ መሰለሽ በወያኔ ጊዜ የታሰሩት? የታሰሩት መጽሐፍቶቼስ ለምን አልተከላከልሺላቸውም? ለምን አጣጣልሺያቸው? ወያኔ ሰብአዊ መብት ታግፍቷል፤ታሪክ አበላሽቷል፤አገር ሸጧል እኮ ነው የሚሉት መጽሕፈቶቼ። ለምን ጠላሻቻው? መጽሐፍቶቼን በታሪክ እንደተመዘገቡና ለትውልድ እንደሚቀሩ ግን አላለማድነቅሽ አውቀትሽ ውሱን መሆኑን ያሳያል። ለነገሩ "አማራ" የጻፈው ምን ይረባሻል? ባንቺ ቤት እኔ አማራ ስለሆንኩኝ ፤ወላጆቼም እንዲሁ 'ያንቺው አይሁዳዊት እና ቤተሰቦችሽ ጠላት ናቸው" ከምትይ ሰው ምን ይጠበቃል? ጣሊያንም እኮ "አማራ ጠላትህ ነው ብሎ ለሕዝብ አስተምሯል።አማራን በመጥላትሽ የኢትዮጵያ አምላክ ይቅር ይበልሽ።

<<ለዚህች ኢትዮጵያ ለምትባል ሃገር አያት ቅድመ አያቶቼ ከሌላው ሀገሩን ወዳድ ኢትዮጵያዊ ጋር ዘምተው በጦርና በጋሻ በጀግንነት ተዋግተው፣ ዳር ድንበሯን በአጥንታቸውና በደማቸው ከማቆየታቸውም ባሻገር፤ እየተዋጉ በመያቸው የተበላሸውን የጦር መሳሪያ እየጠገኑ ላርበኛው መልሶ በማስታጠቅ ተደራራቢ ጀግንነታቸውን ያስመሰከሩ ናቸው። ውለታቸው ግን እርስት አልባ እንዲሆኑና አማራው እንዲጨቁናቸውነ ውየተደረገ ው። >>

አንድ ጊዜ አያቶችሽ የተዋጉላት የሞቱላትን አገር ታደንቂ እና እንደገና የሞቱላትን አገር እያዋረድሽ ታጣጥሊያታለሽ። እንዴ! ታዲያ ለምንድነው አያቶቺሽ ኢትዮጵያዊያን መሆናቸውን እያወቅሽ "አይሁድ ነኝ" ብለሽ አገር እና ማንነት ለመክዳት ያደረሰሽ? አገርሺን ከድተሽ ማንነትሽን ከድተሽ ስለ ኢትዮጵያ ፖለቲካ ማውራቱ፤ ምን ይረባሻል?

ክብርት ወ/ሮ ሃና ፤ እኔም እኮ የምልሽ “እስራኤሎች ለወያኔ እና ለደርግ እንዲሁም ለሻዕቢያ ገንዘብ ሰጥተው አንቺኑን “የዋህ አርግብ” እንዲያሽጋግሩሽ እና በባርነት ገዝተው የኢትዮጵያን ሰንደቃላማ አንዳታውለበልቢ በምትኰ የአይሁዶች ሰንደቃላማ እያውለበለብሽ በኩራት ኢትዮጵያዊት ነኝ እንዳትታይ የሕሊና ሰለባቸው ልትሆኚ ለምን በቃሽ ነው የምልሽ? የወላጆቹን የአያቶቹን ታሪክ ደምና አጥንት ፈስሶ የተገነባው አገር “መከዳት” ወራዳነት አይመስልሽም? ስለ አያቶች ደምና አጥንት ማውራት እና “አይሁድ እንጂ “ኢትዮጵያዊ” አይደለሁም” ከሚለው ጋር አላምታታሺውም?

አንቺ እንዳረጋገጥሺልኝ ስደተኛ እና አንቺ “የዜግንት ወረቀት ሲሰጧችሁ” ልዩነት አለው”። አንቺ ወዲያውኑ አየር ማረፊያ ስትገቢ “የአይሁድ ዜጋ” ብለው ወረቀት ሰጡሽ። ሌላው ያንቺ መልክ ያለው ሱዳናዊ/ኢትዮጵጵያዊ፤ በቅርቡ ደግሞ “ነፃነታቸው ባመጣላቸው ምክንያት” በስደት እና በሲኦል ኑሮ የሚሰቃዩት ኤርትራዊያን እና /ኡጋንዳዊ፤ናጄሪያዊያን ወዘተ,,.... ጥቁር ሰው ግን አንዳንቺው አየር ማረፊያ ወይንም ድምበራቸው ላይ ተንጠላጥለው “ታመፀኑን” “ኣጥልሉን” እያሉ ሲለምኑ ያልተንከባቸው እና እንዲያ ያለ ከበሬታ ያለደረጉበት ምን ምክንያት ሰልላቸው ነው? አይሁዶችን ስለምትመስይ? ኢሕአፓዎች በሱዳን ፤በኬኒያ፤ጁቡቲ፤አሜሪካ.....ስደት ተምችቶአቸዋል የምትይው ቀልድሺን ተይው። ሆ! ሆ! የተመቸሽስ አንቺ!

<<"ሃገሬ ኢትዮጵያ ሞኝ ነሽ ተላላ የሞተልሽ ቀርቶ የገደለሽ በላ" አሉ አርበኞቹ ዘመዶቼ፣ ባንዳ የነበሩት መልሰው ስልጣን ተሰጥቷቸው አዋርደውና እረግጠውሲገዟቸውኖሩ። >>

እነዚህ አርበኞች ዘመዶችሽን የሞቱላትን አገር ከድተሽ እኮ ነው “አይሁድ ነኝ” በማለት ስለምትኩራሪቢኝ እኮ ነው አንቺን አሳንሼ ለማየት የተገደድኩት። ይገባሻል ባንቺ ላይ ያለኝ ቅሬታ? በሕሊናሽ

ላይ እየተምታታብሽ ያለውን "ቀውስ" ማጥራት አለብሽ። አገርሽን መካድ የለብሽም፤ማንነትሽን መካድ አያስፈልግም፤ ነውር ነው። ለዚህ እኮ ነው መጽሐፍት የምፅፈው። አንዳንቺው ያሉትን የተምታታባቸው ዜጎች የሕሊና ድጋፍ እና ጥንካሬ እንዲሆናቸው በማሰብ። አልገባሽም እንጂ አንቺን ከሚያሰቃየው የሕሊና ቀውስ ማምለጫ መሰላል አንዲረዳሽ እኮ ነው ታሪኮቻችንን መጻፍ እየተገደድኩ ያለሁት።ለነሱ አይታወቃቸውም እንጂ ወያኔዎች፤ሻዕቢያዎችም እኮ የዚያ ዓይነት የሕሊና ቀውስ ውስጥ ገብተው ነው እኮ መከራቸው እያዩ ሥልጣን የሙጥኝ ብለው ሲዋዥቁ፤ ሰው ሲገድሉ፤ሲጠልፉ፤ሲወነጅሉ፤ ሲደበድቡ፤ዜጎች ለስደት ሲዳርጉ፤ያገሪቱ ለም መሬቶች፤ንግዶች ሁሉ ጉያቸው ሥር አስገብተው፤በስስት ነቅዘው የማንነታቸው ፍለጋ ቀውስ ገብተው እየተሰቃዩ ያሉት። ልብ ያላለ ሰው ወያኔዎችና ሻዕቢያዎች ስልጣን ላይ ስላሉ "በጤና" ያሉ ይመስለዋል። ሃቁ ግን "ቀውስ ውስጥ የገቡ በሽተኞች ናቸው"

<<ለሃማስ የሚቆረቆርለት ብዙ ያክራሪ እሥላም ድርጅት በዓለም ከፍተኛ ስለሆነ ለፍልሰጤም አትጩኽ ቅላቸው፣ ያንተን እገዛ አይፈልጉም። አንተ መጀመሪያ የራስህን ህዝብና ሃገር ነጻ አውጣ። "አዛኝ ቅቤ አንጓች" ይሏል አንተን ነው። ምነ ውለሰውልጆች እንዲህ የሚያንገበግብህ ከሆነ ለሶሪያ እዘን።>>

አንድ ነገር ላስተምርሽ የምፈልገው ነገር ቢኖር፡ የትም ይሁን ማንም ይሁን ማንም "ሓማስ ይሁን አልፋታሕ፤ወይንም አይሁዶች" በናዚ ሕሊና እና ድርጊት ተነሳስተው ሕጻናትን እና መሮጥ የማይችሉ ሽማግሌዎችን አርጉዞችን የቤት አንስሶችን፤ በአይሮፕላን ቦምብ አንደ በረዶ በማዝነብ የሚገድል "የጫካ ሕሊና" ያለው ቡድን/መንግሥት/ግለሰብ ሁሉ "መቃወም" "ማውገዝ" አንዱ የሰው ልጆች ግዴታ ነው። ሰው የሚያስብለው አንዱ መለያችን የኼ ነው። አንቺም ከዛው ጠባብ የመንደር ሕሊናሽ እንደትወጪ ብትሞክሪ "ሰው የሚያሰኝሽን እና የጣልሺው ኢትዮጵያዊነትሽን" ባህሪ መላበስ

ትቺያለሽ። ለነገሩ አንቺ እኖርበታለሁ የምትይው መንደር እኮ “የጦርነት ቀጠና ነው”። እነሱ “የዓለም እገዛ አንፈልጋለን እርዱን ስቃያችንነ አስተጋቡ” ሲሉን አንቺ “የሕሊና የሰብአዊ ድጋፍ እገዛ አያስፈልጋቸውም” ብለሽ ተናገሪ ብሎ ያስተማረሽ ማን ነው?

እኔም ሆነ አያት ቅድመ አያቶቼ ለ-2500 ዘመን ኢትዮጵያ ስንኖር እስከ እኔ እድሜና ልጆቼ እድሜ ድረስ በተለይ አንተና እናት አባትህ፣ አያት ቅድመ አያቶችህ ይህን ያህል ዘመን ሰው መሆናችን ዘንግታችሁ "ፈላሾች" "ካይሎች' "ሰው በላዎች" ቀን ሰው ማታ ጅብ"፣ ....ወዘተ እያላችሁ ስትሰድቡንና ለዚህች ኢትዮጵያ ለምትባል ሀገር እንዳልተዋደቅንላት እርስትና ሀብት መሬት የላችሁም እያላችሁ ከሰው ሳንቆጠር እንድንኖር ማድረጋችሁን፣ በተለይ እናንተ አማራዎቹ ባለጊዜ የነበራችሁት፣ እንደዛሬ ሳይሆን! ትዘነጋዋለህ ብዬ አላስብም። >>

በጣም የምታሳፍሪ ዜጋ ነሽ። “ለ2500 አመት ኢትዮጵያ ውስጥ ስንኖር” ማለትሽ እኮ “አይሁዶች እንጂ ኢትዮጵያዊያን አልነበርንም ” እኮ ነው እያልሽ ያለሺው። ከዚያስ በፊት (ከ2500 አመት በፊት) የኖሩ ቅድመ ቅድመ..... አያቶችሽ የሉኝም ነው እኮ እያልሽ የምትይኝ? ታዲያ ስደተኛ ነበርኩኝ አንጂ ኢትዮጵያዊ አይደለሁም ካልሺኝ “ራሲሽን በኢትዮጵያዊነት ዜጋ ካልቆጠርሽ” ሓፍረቱ የማን ነው? ትንሽ የሕሊና ሰቀቀን አይሰማሽም? ነጭ አይሁድ ነኝ ስትይ? ስደተኛ ነኝ ብሎ እራሱ የቆጠረ ሰው ቢሰድቡት፤ቢለጉሙት ምን መብት አለው? ታዲያ አንቺው እራስሽ ስደተኛ ነኝ እያልሽ ከሆነ ባለርስቱ ምን ብሎ ርስትና መሬት ያካፍልሽ? ስደተኞች እንደመሆናችን መጠን ከብር አልተሰጠንም፤ ስንሰደብ ነበር ማለት በጣም እራስን የሚያወርድ አባባል ነው። አንቺ ኢትዮጵያዊት ነሽ። አማራ ሰደበን

የምትይው ክስ እስራል ገሬ ነው ብለሽ ቤድሽበት አገር ያሉት አይሁዶቹ ወንድሞችሽ ደግሞ ተቀብለው "ባርያ ነሽ፤አይድስ ተሸካሚ ነሽ" ብለው ሲያቆሹሹሽ ተወቃሹ አማራው ነው?ዛሬም ትንሽ የሕሊና ሰቀቀን አይሰማሺም። ኢትዮጵያ ውስጥ "መኖር" እና "በትውልድ ዜጋ" የተለያዩ ነገሮች ናቸው። አንቺም ሆኑ ወላጆችሽ በደም በአጥንት በባሕሪ በባሕል ኢትዮጵያዊያን ናችሁ። አምነታችሁ "አይሁድ ነው" አይሁድ እምነት መቀበል አንድን ኢትዮጵያዊ "ደሙን እና ቀለሙን መለወጥ አይቻለውም። ነገር ግን ይህ ቅጥፈት እና የማንንት ክሕደት ኤርትራዊያኖች አንዳደረጉት "ቅዠት" አይሁዶች እና ተባባሪዎቻቸው ያንን የምፔሪያሊሰት ኢትዮጵያን የማፍረስ "ሴራ" እንዳንቺው ያለው "የዋህ" ምንም የማያውቅ "እርግብ" ክህደት ውስጥ ገብቶ 'አይሁድ ነኝ" በል ሲሉት/ሰሏት፤ ያንን ክሕደት ተቀብሎ በራስ ቀውስ አንዲፈጥር ምቹ ገበያ ፈጥሮላቸው፤ ይኼው አንቺም "ዜግነትሽን፤ ማንነትሽን ክደሽ" "አይሁድ ነኝ" ብለሽ በተረት ተረት "ተወጥረሽ" ራሲሽን አሞኝተሽ የልጅ ልጆችሽንም "አይሁዶች" አንዲሆኑ በኢትዮጵያዊ ታሪክ እና ማንንት ላይ ከፍተኛ ወንጀል አንደፈጸምሽ ማወቅ ይኖባሻል።

ለሆድ እራስን መሸጥ በጣም አስነዋሪ ባሕሪ እና የኢምፔሪያሊስት ባሕሪ ነው።እንዴት ተመቸሻቸው ልጄ? እነሱም ይህ አይነት ተዋጊ ፍጡር አንደሚፈጥሩ አስቀድመው በጥናት የቀረፁት "እቅዳቸው" ህያው ሆኖ ይሄው "በራስ ፍሊጋ ላይ የገባው ውዥምብር እየተጋባ ያለው ቀውስ " በገራችን ዜጎች ላይ የተካሄደ ዘመቻ፤ የተመቻቸሽ ማስረጃ "ይኸው" አንቺ ሳስተደብቂ እራስሽን ግልፅ አድረገሻል።

በቃ 2500 ብቻ ነው ኢትዮጵያ ውስጥ የኖራችሁት? ያስ ቢሆን ኢትዮጵያዊ ማንነት ለመቅረጽ በቂ እና ከሚገባ በላይ ብዙ ዘመን መኖር ኢትጵያዊ ነኝ ለማለት ከበቂ በላይ በቂ ዘመን እኮ ነው። አንቺ ግን በኮንትራት የመጣሽ ይመስል "ኢትዮጵያ ውስጥ ለ2500 አመት ስንኖር" ሰትይ ጭራሽኑ "የእውቀት ሕሊናሽ እርቃኑን ነው ያወጣሺው"።

ኢትዮጵያ ውስጥ ሰንኖር አማራዎች ‘ጅብ’ ‘ካይላዎች” እያሉ ስድብ ሲሰድቡን ነበር፡ ብለሻል። አንቺ እውነትም ያገርሽን ታሪክ አታውቂም፡ ለዚህ ነው እራስሽን ለመከዳት የተገደድሺው? ‘ካይላ፤ ጅብ’ እያሉ የሚሳደቡት ስድብ በፈላሻ ብቻ የተወሰነ ስድብ አይደለም። እስላሙም ይሳደብ እና ይሰደብ ነበር፤ አማራውም ይሳደብ እና ይሰደብ ነበር፤ አሮሞውም፤ዓፋሩም ኩናመውም፤ ትግሬውም ይሰደብ እና ይሳደብም ነበር። መሰዳደብ “ለፈላሻዎቹ” ብቻ የተወሰነ አይደለም። አንቺ “የወህ ነሽ” ገና ታሪክሽን መማር የማትፈልጊ እራስሺን ‘ለኢምፔሪያሊሰቶች ሽወዳ’ ክፍት ያደረግሽ ተሎ የምትፈርሺ “ወለኻ” ነሽ። ፈላሻ ማለት ስደተኛ ማለት አይደለም። ፈላሻ ማለት ከባሕር ማዶ ፈልሶ የመጣ ኣዲስ መጤ ሃይማኖት ማለት ነው። አይሁዶቹ (ባፈታሪክ) ሃይማኖት ሲያስፋፉ “ የኢትዮጵን ባሕል አፍርሰው/በአይሁዶች ባሕል ተኩት።ይህ እራሱ “በዘመናችን አባባል” ያባሕል ወረርሺኝ ይባላል። የባሕል ወረርሺኝ ሲደረግ “ዜጎች” “ማንነታቸውን ክደው፤ በመጪው ኣዲስ ባሕል እና ማንንት ይቀረጻሉ”። ለዚህም ነው አንቺ በእዛው አዲስ በተደረገልን የባሕል ወረራ ተቀርጸሽ፤ በዛው “አፈታሪክ” ታጥበሽ፤ተገንዘሽ “አዲስ ልብስ ለብሰሽ “አይሁድ ተብለሽ” ፤ ወደ ጋዛ ሰርጥ ተወስደሽ በፍርሃት እየኖርሽ “የጥይት ማብረጃ / ምሽግ እንድትሆኚላቸው ወስደው “በአይሁድነት ያስጠመቁሽ”። ከዚህ ወዲያ ውርደት፤ አሳር፤ ራስን አሳልፎ ለማንም ማንንት መቸርቸር ምን የከፋ ውርደት አለ?

ኢትዮጵያ ውስጥ ርስትና መሬት ለፈላሻዎች እምነት ተከታዮች ብቻ የተከለከለ አልነበረም ። በነገራችን ላይ ፈላሻዎች መሬት ነበራቸው። መንደር ነበራቸው፡ታሪክሽን በሚገባ ተማሪ። ስደተኛ ነኝ ካልሺስ ‘መሬት እና ርስት አልሰጡኝም ማለት ትችያለሽ? ባንዳንድ ቦታ የተከለከሉበትም ለፈላሻዎች ብቻ አልነበረም፤ እሳለሞችም ነበሩ እኮ። አንቺ ብቸኛ ተጠቂ ያደረገሽ ማን ነው? አማራም እኮ ትግራይ ውስጥ በተለይ “አክሱም” ውስጥ መሬት አርስት የለውም። ክርስትያኑም እስላም መንደር ሄዶ ቤተክርስትያን መስራት የመይፈቀዱለት

መንደሮች አሉ። እስላሙም እንዲሁ (አክሱም ከተማ ብቻ) አማራም ከትግሬ በጋብቻ ለጋብቻም በአሳር ነው። ትግሬ ለትግሬ ሆኖም "ደሙ አጥንቱ፤ጨዋነቱ" እየተመረመረ፤እየተቆጠረ፡ ነው የሚጋባው። የተወሰኑ ጕሳዎች ትግራይ ውስጥ መሬት በርስትነት ወይንም በጉልትነት እንዲያርሱ አይፈቀድለትም። ዓፋርም እኮ ትግራይ መጥቶ መሬት አርስት አይቀበልም/አይፈቀድለትም። ሁሉም ጕሳዎች በትግሬነት "ክልል" የተጠሩ ይሁኑ እንጂ ለተወሰኑ ትግርኛ ተናጋሪ ትግሬዎች ብቻ የተከለለ መብት ነው። ማንም ትግሬ ኩናማ መንደር ሄዶ መሬት ማረስ ይችላል። ኩናማ ወይንም ዓፋር ግን አክሱም/ዓድዋ ማረስ አይችልም። የአክሱም ወርቅ አንጠረኞች፤ሸማኔዎች፤ጠላፊዎች፤እስላሞች፤አማራዎች.... ከሕብረተሰቡ ብዙ የስድብ እና የጋብቻ ክልከላ ነበራቸው። ስለዚህ የፈላሻ እምነት ተከታዮች ብቻ ተጠቂ ነበርን የምትይው "ታሪክ አላዋቂነትሽን" የሚያሳይ ብቻ ሳይሆን "ጭፍን፤ገራገር፤የዋህ፤ተላላ፡" መሆንሽንም ያሳያል።

ደግሞ የገረመኝ "እንተ፤እና አባት እናትህ፤ቀድሞ አያቶችህ ካይላ፤ጅብ..." ትሉናላችሁ የምትይው "እሮሮሽን" ሳነብ ባንቺ እስቃለሁ። አንቺን ብቻ ፈላሻ አድርጎ "ፈላሻ ነሽ' ብሎ የኔ አያቶች እና ወላጆች ግን የሌላ ነገድ አምነት ብቻ ተከታዮች ነበሩ ብሎ የነገረሽ ማነው? እኔ ምን መሆኔን በምን ታውቂያለሽ? ምን አይነት ከብት ነሽ? አንቺን መሳይ ኢትዮጵያዊት ከየት ነው የመጣሺው ከእስራል ወደ ኢትዮጵያ? ምኑ ሞኝ ነሽ አንቺ!!? ፈላሻ አይደለህም ብለሽስ እኔን የምታሰምሪበት መብቱ ማን ነው የሰጠሽ? ነጭ አይሁዶቹ ናቸው እንዲህ ብለው የነገሩሽ? እነሱ እነማን ናቸው 'እገሌ ፈላሻ አምነት ተከታይ ነበር እገሌ ግን አይደለም" የማለት በምናቸው ነው ይህ ሁሉ መብት ያገኙት? በላብራቶሪ? የኣለምን ሕዝብ ዜግነት እያስካዱ በዘመናዊ ባርነት የሚያሽጋግሩት ተንኮል ለምን ተቀበልሺው? አንቺ ይህነን ዘመናዊ ባርነት ለምን ተቀበለሽ ሕጋዊነቱን በማረጋገጥ ለምን ተቀበልሽ ? በአይሁድ ዜግነት መኖር እና "ማንንትሽን ሰጥተሽ የአይሁዶቹ ዘር አንጂ ኢትዮጵያ ውስጥ 2500 አመት ብቻ ነው የኖርነው" ማለት "በራስ ላይ መዝመት ነው።"

በጣም ይገርማል!! ደግሞ <<በተለይ እናንተ አማራዎቹ ባለጊዜ የነበራችሁት፣ እንደዛሬ ሳይሆን! ትዘነጋዋለህ ብዬ አላስብም።>> ስትይ ገና አሁን ማንነትሽን በግልፅ አስቀመጥሺሊኝ። በአማራ ጥላቻ እንዲያድርብሽ እና አማራዎች ብቻ ነበሩ ፈላሻዎቹን ሲሰድቡና የፈላሻ መብት ሲጋፉ አማራዎች ናቸው ብሎ አንቺን ያስተማሩሽ “ባስተማሪነት ባሕሪ” አስር ጊዜ የምታወዲሺያቸው “ባርያ” እያሉ “በሁለተኛ ዜጋ” የሚያዩሽ አይሁድ ጌቶችሽ ናቸው እንዲህ ብለው ተከራከሪ ብለው ያስተማሩሽ? አይመስለኝም። ጣሊያኖች ከዚያም ወያኔ ነበር ይህን ቅባት እንደትቀቡት ያደረገው “የፕሮፓጋንዳ መርዝ!፡

ከላይ የጠቀስኩልሽ ሕብረተሰብ በሙሉ የሚሰዳደበውስ ከምን የተነሳ ይመስልሻል? ባልሰለጠነ ማሕበረሰብ ውስጥ መሰዳደብ ያለ ነው; የበላይነት ለማረጋገጥም ይጠቀሙበታል። ለወደፊቱም የሚኖር የሰው ልጆች መጥፎ የባሕሪ እውነታ ነው። አንቺ ወደ እስራኤል ተጭነሽ ስትሽጋገሪ “ደሜ፤አጥንቴ፤ፀጉሬ፤ቆዳዬ፤አይሁድ አገሬ ደግሞ እሰራኤል አንጂ አገሬ ኢትዮጵያ አይደለም ብለሽ እየኖርሽ ያለሽበት አገር “እርስት መሬት ሰጥተውሻል”? ‘ባርያ፤ኤይድ ተሸካሚ’ ብለው አልሰደቡሽም? አንቺን ካልሰደቡሽ ሌሎቹ ይህን ውርደት እየደረሰባቸው እንዳለ የታወቀ ነው። ሌላ ቀርቶ እስራሎች ለኢትዮጵያ የተሰጠው ገዳም ‘ለግብጾች እያዳሉ” በመነኮሳቱ ላይ “ፍርደ ገምድል” እያስተላለፉ አይደለም? ምን የሚሉሽ ባዶ ሕልመኛ ነሽ አንቺ? አንኳን ኢትዮጵያ የረገጥሺበትን የእስራል መሬት ገና የእግርሽ ኮቴ ገና ሳይደርቅ አይደለም እንዴ “መብትሽን መግፈፍ” በቆዳሽ ማላጋጥ የጀመሩት? እረ ተው እናንተ ኢትዮጵያዊያን ኢትዮጵያን መንከስ፤መርገም ይቅርባችሁ? አጥብታ ያሳደገች አገር ጡት ለምን መንከስ አስፈለጋችሁ? የናት ጡት መንከስ “ሃጢያት እና ነውር መሆኑን” መገንዘብ ለምንድነው ያቃተሽ?

<<እሥራኤል ያለው አብዛኛው ቁጥር ይሁዲ የመጣው

ከአፍሪቃና ከኢስያ ነው። ምሳሌ ብጠቅስልህ-ሞሮኮ፣ ሊቢያ፣ ኢትዮጵያ፣ ግብጽ፣ ኢራን፣ ኢራቅ፣ ሶሪያ፣ ሊባኖስ፣ ቱርክ፣ ቱኒዚያ፣ ህንድ፣ ስፔን፣ ....ወዘተ ከአወሮፓውና ከምእራቡ ዓለም የመጣው ቁጥሩ ከዚህ ያንሳል። ማለት የፈለኩት ከላይ ከጠቀስኩት ቀፋፊ ስድብ የበለጠ እዚህ አይሰድቡንም። ቢሰድቡን መብታችን በፍ/ቤት እየከሰስን በማስቀጣት እናስከብራለን፣ ሰላማዊ ሰልፍ በመውጣት በህግ እናስደነግጋለን።>>

የተሸጠው ቁጥር ብዛት ስትነግሪኝ ለኔ ያሳዝነኛል እንጂ ምንም አይረባም። እስኪ ልጠይቅሽ፤- 'ስድብ ሸሽተሽ ወደ ስድብ መሄዱ አገር ስትሄጂ የሚያስተምርሽ ነገር ምንድነው ብለሽ ራስሺን ጠይቀሽ ታውቂያለሽ?" ስድብ በማንም ዓለም ሕብረተሰብ ውስጥ የኖረ ፤ የሚኖር የሰው ልጆች የደነዘ/የደነቆረ የሕሊና ውጤት መሆኑን ነው የሚያስተምርሽ። ያ ከሆነ አንቺ ለከዳሺያት 2500 አመት ብቻ ኖረንባታል የምትያትን ለኢትዮጵያ ብቻ "ተወሰነ" ባሕሪ እንዳልነበረ ነው የሚያሳይሽ። ስለዚህ "አማራዎች" ሰደቡን እያልሽ የምትከሺው ክስ "አይሁድ ነኝ" ብለሽ ወደ ፈረንጆቹ አገረ እስራል ተጭነሽ ስትሽጋገሪም እዛው ጠብቆ ካናወጠሽ እና የፈረንጆቹ የአይሁዶቹ "ስድብ ወድደሽ ሳትወጂ ከተቀበልሽው" ኢትዮጵያን ብቸኛ ተከሳሽ እና ዜግነት እስከመቀየር የሚያደርስ ምንም ነገር አልነበረሺም።

ስለ ሰላማዊ ሰልፍ መብት የሚመለከት ባነሳሺውም ቢሆን፤ኢትዮጵያ ውስጥ ለፈላሻዎች ፤ላንቺ ብቻ የተከለከለ አልነበረም። ለሁሉም ዜጋ የተከለከለ ነው፤፡ ድሮም አሁንም። ይህ እንዴት ሲሆን ነው? እያወቅሺው ጠፍቶሽ ነው? "እስራል ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግ" ይፈቀድልናል፤ ኢትዮጵያ ግን 2500 አመት ስንኖር አለተፈቀደለንም፡ የምትይው? ላንቺ ብቻ ተከልክሎ ለሌላ የተፈቀደበት ምን "መረጃ" ልትሰጪኝ ትችያለሽ? ለክህደቱ ሽፋን ግን "ጥሩ ጉዝጓዝ" ይሆናል

የምትይው መሸፈኛ “ስድብ” ግን እስራኤልም ሄደሽ በዘረኛ አይሁዶችም በኩል ስድቡ “ከተከተለሽ” ስድብም (ያውም በሕጻናት ልጆችሽ ሲፈጸምባቸው) ስትታዘቢ “ወደ ሕግ” ከመሮጥ “ወልዳ ወደ አሳደገቺሽ እናት አገሪሽ ኢትዮጵያ” ብትሮጪ እና ማንነትሽን ለማስከበር ብትታገይ አማራጭ የሌለው አዋቂነት ይሆን ነበር።

ለመሆኑ ምን የሚሉሽ ማሰብ ያቆምሽ ፍጡር ነሽ? እስኪ ይህን ተመልከቺ። እስራኤሎች ሲሰድቡን ወደ ሕግ ወስደን እናስቀጣቸዋለን የምትይው ነገር ሞኝነትሽን አሳቀኝ። እስራሎች ናቸው ስለ ስደተኛ (እንዳንቺው ያለውንም በራስ ማንንት ቅውስ የተመቸውም ጭምር) ሕግን የሚያስከብሩ? የእስራኤል አገር ውስጥ ሚኒስቴር እንደ እነ Eli Yishai የመሳሰሉት ጸረ አፍሪካ/ጡቁር ጠሊታ ግለሰዎች ናቸው ሕግ አስከባሪወች ናቸው የምትይው? ምን እሚሉሽ የዋህ ነሽ? ዓረቦች እና እስራኤሎች ዓለም ያወቃቸው “ጡቁር የሚጠሉ፤አፍሪካን የሚጠሉ” ዘረኞች/ጠበብ ያሉ መሆናቸው አንቺ አታወቂውም ማለት ነው? ካለ ዘራቸው ሌላ ለጋብቻ ማሰብ እንደሚከብዳቸው አታወቂውም? አንድ ነገር እውነት ነው። ይኼውም፤-በማንነት ቀውስ የሚሰቃይ ሕሊና በራሱ ላይ ሲዘመትበት “አይታወቀውም።” ለዚህ ነው አንቺ ስለ እስራኤሎች “ሰላማዊ ሰልፍ እና የዜጋ አክባሪነት” እንደ ሽፋን መከላከያ እየነገርሺኝ ያለው።

<< ልጆቻችን ከሁዋላ ቀር ሃገር የመጡ ተብለን ለማንም የማይሰጠው እገዛ እተደረገላቸውና መንግሥት በብዙ ሺህ ብር እየከፈለላቸው ዩኒቨርስቲ እንዲማሩና ከሌላው ህብረተሰብ ጋር እኩል ዲግሪ እንዲይዙ ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል። >>

እንዳንቺው ያለ ባርነትን የተመቸው ማፈሪያ ሰምቼ አላውቅም። ምን እሚሉሽ ግራ የተጋባሽ ነገር ነሽ? “ዴፖ ፕሮቬራ” የተባለ የወሊድ መቆጣጠሪያ መድሃኒት ለኢትዮጵያዊያን ሴቶች በምስጢር ለምን እየተሰጠ እንደነበረ ልትነግሪኝ ትቺያለሽ? አንቺ ክሕደት ውስጥ ስላለሽ አልገባሺም፡ ነገር ግን ሰነዱ የሚነግረን ደግሞ ይህን

የሚከተለው ነው። **Israel's Treatment of Ethiopians Called 'Racist'.m4v**
http://youtu.be/LrOMDZt2xeo
ይህንን ጉድሽ ተሸክመሽ ነው ደግሞ “መብት አለን” ዩኒቨርሲቲ ይፈቀድልናል ምንትስ የምትይው? ምን እሚሉሽ ማፈሪያ ነሽ አንቺ?
**Ethiopian Jews blame Israeli racism for discrimination and price tag graffiti in Kiryat Malakhi**
**http://youtu.be/p_acfNfFkgw**

ይኼ ነው በእስራልነት ተቀርጸን ፤የአላማ አንድነት አለን የምትይው “ቀረጻ”? “ዘመዶችሽ ገላ ላይ “ዘረኝነት ሲሰነዘርባቸው፤ በህጻናት ላይ የቀለም ልዩነት ሲፈጸምባቸው፤አፍሽን ሞልተሽ “የአንደንት አላማ አለን፤ በእስራላዊነት ተቀርጸን” የምትይው “የሕሊና ቀውስ” ሲደርስባችሁ ኢትዮጵያ/አማራዎች “ካይላ፤ጅብ” እያሉን ነበር እያልሽ ኢትዮጵያን እና አማራን” ስትወነጅሊ የእስራል ውርደት ጋር ስታነጻጽሪ ትንሽ አታፍሪም?

ኢትዮጵያዊያን አየደለንም ትያለሽ እንደገና “ርስት መሬት” አንዳይኖረን አማራዎች ከለከሉን ትያለሽ፤ እሰራኤልስ እየደረሰብሽ ያለው ልትደብቂው ነው? “አፍሽ ሞልተሽ” አማራ እንዲህ አደረግን ብለሽ የምትከሺው? አማራው እንዲህ ያለ እርኩስ ስራ ያውም ከላይ የሰጠሁሽን “በሴቶች ማሕጸን “ሴራ” እስራል ውስጥ ሲፈጸም ኢትዮጵያ/አማራ ይህ ሴራ ፈጽሞብሻል? ምን ክሕደት ውስጥ ነው ያለሺው የኔ እህት?

<<የዓላማ አንድነት ከህጻንነት ጀምሮ ስላለ፣ በእሥራኤላዊነት ታንጾ እንዲያድግና ከምንም በላይ ሀገሩን እንዲወድና እንዲያከብር ሆኖ ያድጋል።>>

በስመ አም! አንቺ ትንሽ አታፍሪም? ጡቁር ህጻን አንዳይባዛ ከላይ የሰጠሁሺን መረጃ “በእስራላዊነት” ሞራል መገንባትና ማነፅ ማለት ይኼንን ተግባራቸው ነው? ይህ የደቡብ አፍሪካ ዘረኞች እና የናዚዎች ስራ በኢትዮጵያዊያን እህቶች ማሕጸን ሲፈጸም “አሜን” ብለሽ

ተቀብለሽ ከላይ የሰጠሁሽን አጸያፊ መረጃ ስታወድሺ ማየቴ አዲስ አይደለም።

ጥቁር አሜካዊው የነፃነት ታጋይ “ማልካም ኤክስ”። (ሃውስ ስሌብ) (የቤት ባርያ) የሚለው ስንኝ ነበረው። የቤት ባርያ እና የማሳ/እርሻ ባርያ (የፋርም) የሚባሉ የባሪያ ባሕሪ ገለፃዎች አሉ ይላል። በባርነት የሚያስተዳድረው ገዢው ሲታመም “ከገዢው ይልቅ ይበልጥ የሚታመመው፤ “የቤት ባርያው” ነው (ለኔ ያረግልኝ፤ካንተ በፊት ልደፋ፤ አንተን የሚወቅሱ ይረገሙ፤ይላል። ፍርፋሪው እንዳይቀርበት ማለት ነው) ። የማሳ/የፋርም ባርያው ግን “ገዢው ሲታመም” “ተሎ በወሰድህ፤ተሎ በሞትከልኝ” ይላል። ይል ነበር። እኔ የማውቃቸው ሌሎቹ “በኢትዮጵያዊነታቸው ፀንተው አገራቸውን የሚያከብሩ አይሁዶች ኢትዮጵያዊያን ግን” ካንቺው እምነት በጣም የተለየ “ለእናት አገራቸው ኢትዮጵያ እና ለማንነታቸው ልዩ ክብር ያላቸው “የአይሁድ ሃይማኖት” ተከታዮች የማውቃቸው እዛው እስራል ውስጥ አሉ።”ዘረኝነትን የትም ይሁን የትም የሚዋጉ፤ የሚኰንኑ”። አንቺ ግን የሌለን ታሪክ እያመጻደቅሽ ኳኩለሽ ስታቀርቢላቸው “ግብዝነትሽና ክሕደትሽ” ወሰን የለውም። ደግሞ “ለአማራ ያለሽን ጥላቻ” ስመለከት ላንቺ “አዘንኩኝ”። የሚከተለው ነገር ስትይ ይበልጡኑ አስገረመኝ።

<<እዚህ ሃገር አንዳንድ ሰዎች ሲናደዱ "ኩሺ" እና "ኢትጿ" ነው የሚሉን። ስንበልጣቸው፣ ያውም ያልተማሩት ናቸው፣ የጉልበት ስራ የሚሰሩት። >>

እኛን የሚሰድቡን ያልተማሩት “ሽቃዮች፤የጉልበት ስራ የሚሰሩ” እንጂ የተማሩት እስራሎች ግን ያከብሩናል” ስትይ በጣም አሳፋሪ ሕሊና ነው ያለሽ። “የዘረኝነት ባህሪ” ባልተማረው እና በተማረው መካካል አጥር አያደርግም ። የተማሩ ናዚዎች፤ሳይንቲስቶች ናቸው እኮ “አይሁዶችን የጨፈጨፉት”። የተማረ እስራኤላዊ ዜጋ “ዘረኝነት አያንጸባርቅም” ስትይኝ “ምን ያህል ድንቁርና እንደተጫነሽ አመላካች ነው። ዘረኝነት ትምህርት አያውቅም። ዘረኝነት የተማረውንም

ያጠቃል።ዘረኝነት “ጥላቻ ነው” አንዱ ዲግሪ ስላለው አንዱ ሽቃይ ስለሆነ አይደለም የሚመነጨው። (ከልጅነት ጀምሮ “ሚስ ጋይድድ” የሆነ ካልተገራ ሕሊና ነው የሚያመነጨው።) ወይ ጉድ። ያልተማረውን “ሽቃዩን” የጉልበት ሰራተኛውን” ብቻ ለምን ጠመድሺው የኔ እህት?የተማረውን እስራላዊ ዘረኛ የለም ስትይኝ፤ የምትኖሪበት አገርም የምታዉቂው አይመስለኝም።

<<እዚህ ሃገር አንዳንድ ሰዎች ሲናደዱ "ኩሺ" እና "ኢትጵ" ነው የሚሉን።ስንበልጣቸው፣ ያውም ያልተማሩት ናቸው፣ የጉልበት ስራ የሚሰሩት።>> አልሽ? በዚህ ንግግርሽ ስላንቺ ባለ ዲግሪ ትምህርት አፈርኩልሽ።

<<የዓላማ አንድነት ከህጻንነት ጀምሮ ስላለ፣ በእሥራኤላዊነት ታንጾ እንዲያድግና ከምንም በላይ ሀገሩን እንዲወድና እንዲያከብር ሆኖ ያድጋል።>>

በእስራላዊነት ዓላማ ታንፃችሁ እንድታድጉ ከተደረገ “ያልተማረው ሽቃዩ” የምትይው አንዴት በእስራላዊነት ሳያንጹት አንቺን እና ልጆቺሽን ሊያንጹ ጓጉ? አንቺን ሲያስተምሩ ሽቃዮቹ ዘረኝነት እንዲያስወግዱ በእስራላዊነት ሳያንጿቸው እንዴት ቀሩ? ቀልደኛ ነሽ አንቺ!

<<ከዚህ ሃገር የማይፈልጉት ከሱዳንና ከኤርትራ በሲናይ በረሃ የገቡትን ስደተኞች እንጅ፣ እኛንና ኢትዮጵያዊ ስደተኛውን እንኳን አይደለም። እነሱንም የጠሏቸው ከዚህ በሚሰሯቸው በጣም አጸያፊ ስራዎቻቸው፣ የተቀነባበረ ሌብነታቸው፣ ለገንዘብ ብለው የሚፈጽሙት የነፍስ ግድያና ሴቶችን አስገድዶ መድፈር የመሳሰሉ ድርጊታቸው ዜጋው ህብ/ሰብ

ልጆቹንና ሚሰቶቹን ሲወጡና ሲገቡ ጠብቆ መቀበሉ ስለሰለቸው ነው። እነሱ ይህችን ሃገር ከረግጡጊዜ ጀምሮ ዜጋው በገዛ ሃገሩ ባይትዋርነት ስለተሰማው ነው። >>

ምን ዓይነቱ ዘረኛ ነሽ አንቺ? ይህ ሁሉ ከሲናይ እና ከኤርትራ ከኢትዮጵያ መከራቸውን አይተው፤ ሴቶች እህቶቻችን በሰሓራ በረሃ “በበደዊን” አውሬዎች እየተደፈሩ፤ “ፅንስ ይዘው” በባርነት ተይዘው አምልጠው “የሰው አገር ነው” ብለው ወደ እስራል መጠለያ ሲጠይቁ፤ “አንቺ ደግሞ” ሌቦች ዘራፊዎች ወንጀለኞች ናቸው። ስትይ ትንሽ ለሕሊናሽ አታፍሪም? ሴቶች እህቶች እንዳንቺው ወጣቶች በበደዊን የዓረብ አውሬዎች እየተደፈሩ፤ በእሳት እየተቃጠሉ መጠለያ ሲጠይቁ “አንቺ” በምን ሞራልሽ ነው እነዚህን ሰዎች “በሌብነት፤ በወንጀኛነት” እየከሰስሽ” የዘረኞቹ “አጨብጫቢ” ፕሮፓጋንዲሰት የሆንሺው? ከኢትዮጵያዊያን ስደተኞች እና “እኛ’ ብለሽ እራሲሽ ከኢትየጵያ ስደተኞች የምትለይው “አይሁድ ኢትዮጵያዊያን” የምትያቸውንስ በወንጀል የተሰማሩ፤ “በእፅ፤በሓሺሽ እና በመሳሰሉ” የተሰማሩ ሱሰኞች፤ ሌቦች የሉም? ትንሽ አንኳ አንደ ስደተኛነትሽ (አንቺ አይሁድ እንጂ ስደተኛ አይደለሁም ብትይም) ዞር ብለሽ ሕበረሰተቡ የገባበት አዲስ ባሕሪ እራስሺን “መፈተሽ” አትሞክሪም? ያ ባሕሪ ከጎንደር ይዘውት ነው የመጡት ልትይኝ ነው? ድሮ አይሁድ ነሽ ስለተባልሽ “እነዚህ አፍሪካዊ ፤ኤርትራዊ፤ሱዳናዊ፤ኡጋንዳዊ... አፍሪካዊያን “ሌቦች፤ወንጀለኞች” ብለሽ ስትከሺያቸው፤ ትንሽ ሞራልሽ አይነካሺም?

ይህ ሁሉ ሺሕ ስደተኛ “ሌባ ነው? ወንጀለኛ ነው? የአይሁድ ዘረኞች ኤርትራኖቹ ንግድ ቤት “ሱቅ፤ ንግድ” መስርተው የሚኖሩ ኤርትራዊያኖች ጋር ሄደው ንግዳቸውን በእሳት ሲያጋዩ በድንጋይ ሲቀጠቁቷቸው፤ “ወንጀለኞች ስለነበሩ ነው? ምን እሚሉሽ ማፈሪያ ነሽ? አንዳንቺው ያሉት ከኤርትራ፤ ከሱዳን፤ ከጐንደር የተሰደዱ በሲናይ በረሃ የመጡ “ ስደተኞች” ወንጀለኞች ናቸው እና ከእስራል ምድር ይውጡ፤ለስቃይ ይዳረጉ ስትይ ለፈጠረሽ አምላክ “ትንሽ

አታፍሪም”? ደግሞ እስራል አገር ውስጥ የገቡትንም ጭምር እኮ አይደለም የሚያባርሩት ፤ዝርፍያ ላይ ያልገቡትንም እኮ ነው ድምበራቸውን ዘግተው ወደ ሞት እና ወደ ጨካኞቹ ዓረቦች ወደ ግብፆች አንደገና ወደ ቦደዊኖች እንዲመለሱ ድምበራቸወን ሳይሻገሩ አግደው ወደ ሌላ ሞት እና ስቃይ የሚመልሷቸው! አይገባሽም እንዴ ዘረኝነት ምን ማለት አንደሆነ? መጠላያ የሚከለክል አገር በዓለም የተወገዘ መሆኑን አልተማርሺም? ምን እሚሉሽ በስደተኞና ሴቶች እህቶቻችን ሕይወት የምትፈርጂ ጨካኝ ነሽ አንቺ?

<<በእነዚህ ህብ/ሰቦች ምክንያት ሆስፒታሎች እየቆረቆዙና የመታከሚያ አልጋዎቹን በማሰሩት የወንጀል ስራዎቻቸው ስለሚያዙ፣ ሃኪሞችና ሆስቲታሎች ዜጋውን ማስተናገድ ስለተሳናቸው ህዝቡ ግብር እየከፈለ በገዛ ሃገሩ ህክምና እንኳን ሊያገኝ ባለመቻሉ ነው፣ ኤርትራውያንና ሱዳኖች ይውጡልን የሚለው። ይህ ደግሞ ጥቁር የማይወድ ህዝብና ሃገር አያስብልም። እዚህ ያለውን እዚያ ሰለማታይ አልፈርድብህም። >>

ወይ ጉድ! አንቺየ ምን የሚሉት ትምሕርት ነው ያስተማሩሽ ? ይህ ሁሉ ሰው የእስራል ሆስፒታል በማራቆቱ ነው ወደ ማጎርያ (ኮንስነትረሺን ካምፕ) እየታጎረ እንዲመለስ እየተደረገ ያለው? በጣም አስገራሚ ሕሊና ነው ያለሽ። የኔ እህት ብዙ የተጣመመ ሕሊና ስላለሽ ‘የሳይኪአትሪክ/ስነ ኣኢምሮ እና የስነ ሕሊና ሊቃውንት ጓደኞቼ ዶክተሮች አሉ እና በስልክ አነጋግሬ፤ ችግርሽ ምን እንደሆነ እንዲያነጋግሩሽ ለማድረግ ፈቃኛ ነኝ” አንቺ ፈቀደኛ ከሆንሽ” ይህ የጤንንት አይመስለኝም። የተጣመመው አስተሳሰብሽ እንዲስተካከል ፍላጎቴ ነው። በጣም የተጠናነገ፤ሥር የሰደደ፤ ጸረ ጥቁር ስደተኛ ሕሊና እንደዚህ አላየሁም። አንቺ ጥቁር ነሽ ፤እንዴት ሁሉንም በሺሕ የሚቆጥር ስደተኛ “ሆስፒታል አራቋኞች” ናቸው እና “መታሸግ

መሰደድ፤መጠረዝ፤መባረር” ይገባቻዋል” ትያለሽ? ዘረኞቹ አይሁዶች “ይውጡልን የሚሉት” የአፍሪካ እና የጥቁር ጥላቻ ስላላቸው ነው። አፍሪካኖች አውሮጳን አበላሽተዋታል እና “እስራልም” እንደ አውሮጳ “በቆሻሾች አፍሪካዊያኖች” አንድትበላሽ አንፈቅድም እና ‘ይውጡልን” ነው የሚሉት። እዛው እኖራለሁ ትያለሽ፤ ስጋሽ እንጂ ሕሊናሽ እዛው አይኖርም። እስኪ ትዕግሰት አድርገሽ ይህንን መረጃ ተመልከቺው።

**The Stream: In Israel, African migrants under attack**
[http://youtu.be/_rW6uNUMEmo](http://youtu.be/_rW6uNUMEmo)

ከዚህ ውይይት ምን ትመሪያለሽ? የእስራል ሆስፒታል የሚዘርፉ ስደተኞች ናቸው እነዚህ?

<<አታወቂ ይሆናል እንጂ ጋዜጠኛ ይገደላል ነው ያልከው፤ ጉድ!!ጉድ!! ያስብላል ይህስ። ሩሲያ መሰለህ?ወይስ ኢትዮጵያ?>>



ብለሻል በሰላው ውሸትሽ።ይህች አሜሪካዊት ጋዜጠኛ የተገደለቺው ሩስያ ውስጥ ወይስ ኢትየጵያ ውስጥ ነው? በቡልደዘር በናንተው ወታደሮች ጋዛ ውስጥ በግፍ

የተገደለቺው ምን ሕጋዊነት ይኖሮዋል? ልትነግሪኝ ትችያለሽ? ምን እሚሉሽ አስገራሚ ነሽ አንቺ? በዚህ ብዙ ጋዜጠኞችን ልጠቅስልሽ እችላሉ።

<<አኔ የዚህችን ሀገር መሬት አየር ማረፊያ ላይ እንደረገጥኩ ነው ዜጋ የሚለው መታወቂያ ያለልመናና ደጅ ጥናት የተሰጠኝ። ግሪን ካርድ፣ ዩ.ኤን.ኤች.ሲ.አር፣ ሁማና ራይትሰ ዎች፣ .....ወዘተ ብዬ ለምኜና የሆነ ያልሆነውን ቀባጥሬ አይደለም የተቀበልኩት። >>

አንቺ አፍሪካዊ አይደለሁም “ይሁዳ ነኝ” ብለሽ እስራል አገር ስትደርሺ ‘አየር ማረፊያ ላይ”፡ ወረቀት ሰጥተው ስለገባሽ ያለ ምንም ችግር አይሁድ ሆንሽ። አይሁድ አይደለንም “አፍካዊያን፤ ኢትዮጵያዊያን፤ሱዳናዊያን፤ኡጋንዳዊያን፤ናጄሪያዊያን ነን” ብለው ማንነታቸውን ጠብቀው “ለመኖርያ ግሪን ካርድ አይሁዶቹን ቢለምኑ ታዲያ ምን ነውር አለው? ትንሽ ለሰው ሳይሆን “ላንቺ” ክብር ብለሽ ለሰው ልጅ፤ለስደተኛ ያለሽ ንቀት “ብትቀንሺ” ምን አለበት። ከሲኦል፤ከችግር፤ከሰሓራ፤ከሲናይ በረሃ፤ከአመጽ፤ከባርነት ሸሽተው አርግዘው የሚመጡትን እህቶቻችን “መጠላያ” ለማግኘት “ቢቀባጥሩ ቢለምኑ” አንቺን የሚያኩራራ እነሱን ዝቅ አድርጎ አንደትመለከቺ ያደረገሽ የዘረኝነት የደንቁርና በሽታ “ምንነትሽ ላይ ከእነሱ ልዩ ያደረገሽ’? ብዙ የዋህ ጋር ተከራክሬአለሁ፤ አንዳንቺው ያለው መስመር የዘለለ፤ ለወንድም እና እህቶቻ/ወንደሞቿ ስደተኞች ፡”የሚንቅ’ ሰው ገጥሞኝ በሕይቴ አላውቅም። በዚያም አስፈሪ ፣ ምጥቀት ነው፤ ያለሺበት ሕሊና። ሥልጣን ብትይዢ እንዚህ አፍሪካዊያን ምን ታደርጊያቸው እንደነበር ሳስበው ያስደነግጣል።

<<(እኛ የሰራነው) ዛሬ ዘመዶችህ ሲንቁት የነበረውን ምጣድና ድስት ይሰሩ ገብተዋል። ሲንቁን የነበረው ዛሬ ከእኛ ጋር ለመጋባት እሽቅድድሙን ታውቀዋለህ ብዬ እገምታለሁ። እና አንተን ያንገበገበህ ወያኔ

የ ወሰደው ገንዘብ?ወይስ እኔን ዜጋዬ ብላ ሳልንገላታና ሳልለማመጥ የእሥራኤልን ምድር ስረግጥ ዜግነት መቀበሌ ነው ያንገበገበህ? >>

<<ድሮም በእወቀታችንና በመያችን ኢትዮጵያን ጠቅመናት ኖረናል፣ ሰንሄድም በገንዘብ ጠቅመናት ሄድን ። ? >>
ዘመዶቼ አናንተን ለማግባት ሲሽቀዳደሙባችሁ እሺ እያላችኋቸው ወይንስ ያው “አይሁድ ላይሁድ ብቻ ነው የምንጋባው” እምቢ አላችኋቸው? እናንተን ለማግባት ሲሽቀዳደሙ አንቺ ማንን አገባሽ? አይሁዳዊ ወይስ ዘመዶችህ የምትያቸው “አማራዎችን” ነው ያገባሺው? ይህን ታሪክሽን ብትነግሪኝ በጣም አመሰግንሻለሁ። ለምንስ ነው አንተን ለማግባት “እሽቅድድም ውስጥ የገቡት”? ልትነግሪኝ ትችያለሽ? እንደ ሁለተኛ ዜጋ ስለማትታዩ ይሆን? እስራኤል አገር ውስጥ በጥገኝነት ሲኖሩ በናንተ ተጠልለው “ከዘረኝነት ስድብ እና ጥቃት እንድታድኗቸው ነው እናንተን ለማግባት እየተሽቀዳደሙባችሁ ያሉት? ወይስ “ቆዳችሁ ወደ ነጭነት ስለተለወጠ? እራስሺን ከዘረኞች አይሁዶች ጥቃት እና ውርደት ሳትድኚ “የኔን ወገኖችን ከጥቃት ስለማድናቸው ነው እየተሽቀዳደሙብን ያሉት ካልሺኝ” ከመገረም አልፌ ፣ምን አንደምል እውነት አሁን እየጨነቀኝ መጥቷል። ወይ ጉድ።

የእጅ ጥበብ ምጣድ እና ድስት አስተማርናችሁ አልሺኝ። ታዲያ ያ ባለ ሙያነትሽ ከእስራል ነው የመጣው? ሞያ የምትይው እስራሎች ወደ ኢትዮጵያ ያመጡትን “የምጣድ እና የድሰት ስራ ነው” ብሎ ያስተማረሽ ማነው? አይሁዶች የጤፍ አንጀራ “በሙጌጎ/ከሸክላ አየተሰራ ምጣድ” እየጋገሩ ይበሉ ነበር ያለሽ የትኛው ሊቅ ነው? በየትኛው የታሪክ መጽሐፍ ነው ጤፍ እስራል ውስጥ ይበቅል ነበር

እና ሙጌጌውም/ፃሕሊ (የእንጀራ መጋገሪያ እና ወጥ መስሪያ ምጣድ ድስት) እዛው ነበር የተፈለሰፈው ያለሽ? አንቺን እንዲህ ሲል ያስተማረሽ ማን ነው? "ልታብራሪሊኝ ትችያለሽ"? አይሁዶቹ ዓለም እንደሚያያቸው "ነጮች እንጂ ጡቁሮች አይደሉም"። የሚመገቡት እና የሚሰሩበት ምጣድም ያው የፈረንጆች ባህል ነው። ሙያቸውስ ተይው "ቆዳቸው እና ጸጉራቸውስ ባንቺ ፀጉር እና ባንቺ ቆዳ ለምልክት እንኳን የለም። የለሰለሰው ፀጉራቸው ፤የዓይናቸው ቀለም፤ እና ፈረንጅ ቆዳቸው ሳትላበሺ /ባንቺ ላይ አንኳ ለምልክት ሳይኖር/ሳይተውልሽ እንዴት ከአፈር የተሰራ መጌጌ/ምጣድ/ድስት "ሞያቸውን ብቻ" ወዳንቺ አስተላልፈው ኢትዮጵያን በድሰት ስራ ሙያ በሞያ አንድታሳደጓት ሽክላውን ብቻ አስይዘው ላኳችሁ? "የድስት፤ምጣድ ስራ" ሙያ እንድታስተምሩን ሲልኩሽ (ያንቺ ቅድመ ዘመዶች ማለት ነው) ቆዳ እና ፀጉር ሳይተውልሽ እንዴት "አይሁድ ነኝ" ልትይ በቃሽ? ትንሽ እንኳ ምልክት ምነው ካንቺ 'የሰራ አካለት' ለምልክት ሲታይ አልቻለም? ልትነግሪኝ ትችያለሽ? ለምን ቆዳቸወን፤ ጸጉራቸውን ንጥረ ፍጥረት እንዳላስተላለፉልሽ? ዓለምም ሆነ እነሱ የሚነግሩን "አይሁድ ቀለሙ ነጭ እንደሆነ ነው የምናውቀው እና እነሱም የሚነገሩን"። የሞጌጌ/የድሰት ስራ አስራላዊ ነው ብሎ የነገረሽ "ሊቅ" ግን ብትነግሪኝ ደስታወን አልችለውም፤፡

ደግሞ <<አንተን ያንገበገበህ ወያኔ የወሰደው ገንዘብ?ወይስ እኔን ዜጋዬ ብላ ሳልንገላታና ሳልለማመጥ የእሥራኤልን ምድር ስረግጥ ዜግነት መቀበሌ ነው ያንገበገበህ? >> ስትይ 35 ሚሊዮን ዶላር የተሸጥሽበትን መደለያ ነው ኢትዮጵያን ጠቀምናችሁ እያልሽ የምትቀልጂብን? ምን አይነቱ ነውረኛ ነሽ አንቺ? ራስሽን አይሁድ ማድረግ እና ለዘረኝነት ተጋልጠሽ መኖር ያንቺ መብት ነው። ያንን ውርደትሽን ምቾት ነው ካልሽ ጥሩ ይመቺሽ። ነገር ግን ሌሎች አፍሪካዊያንን ሌቦች ፤ዘራፊዎች እያልሽ መዝለፍሽ ግን "የደንቆሮ ደንቆሮ ፤ራሷን ማወቅ የተሳናት ግብዝ እንዳንቺው ያለው "የፈረንጅ አለቅላቂ 35 ሚለዮን ዶላር የዘመናዊ ባርያዎች ንግድ የደላለ ሽያጭ

እና እኔ ጋር ምን የሚያገናኘው ነገር አለና ነው “እኔን” ከሽያጩ ጋር እና ከደላሎቹ ጋር የምታገነኚኝ? ትንሽ አታፍሪም? እኔን ያንገበገበኝ አንቺ የተሸጋገርሺበትን ለደላሎች የተሰጠ ገብዘብ ሳይሆን (ያንን ላንቺ ያሰምምሽ አንጂ እኔ ጋር የሚያገናኝ ነገር የለኝም) አፍሪካዊያን ጥቁር ስደተኛዎችን መጥለትሽ እና ዘራፊዎች የምትያቸው “የአይሁዶችን ሆስፒታል ያራቆቱ” ብለሽ ከሲናይ በመከራ የመጡትን አርጉዞች ሳይቀሩ “ሌቦች” “ወንጀለኞች’ ናቸው፤ የምትይው “ዘረኛ እና ድንቁርናሽ” ነው ያንገበገበኝ ያስቆጣኝ። በስርአት እስራላዊነትን አነፁኝ የምትያቸው መምህራኖችሽ ባፍሪካዊያኖች ላይ ያወረዱት አንቺው የምትደግሚው ዘረኝነት እስኪ “አንድ ጀግና ጥቁር አፍሪካዊ ለመምህራኖቺሽ” እና ላንቺ መሰል “ጡቁሮችን የሚያንኳስሱ” ሰዎች ምን ብሎ እንደመለሰላቸው ፤ይኼው አነሆ አድምጪው።**Racism vs. Africans in Israel (1/4)** **[http://youtu.be/rYwvGHY1nAI](http://youtu.be/rYwvGHY1nAI)**

ስለ እኔ ለማወቅ እኒ አቤ ቶከቻውን፣ እኒ ተመስገን ደሳለኝን መጠየቁ በቂ ግንዛቤ እንድትጨብጥ እገዛ ይህ ሁኔታ በጣም ያረካኛል።እኔ እድገቴም ኑሮዬም <<ጳጉሜ 3 ቀን 1982 ዓ/ም ኢትዮጵያን እስከለቀቅሁበት ጊዜ ጎንደር ነው። "ሐና መከተ"ን የምታዉቁ ካላችሁ ብለህ ብትጠይቅ የሚሰጥህ መልስ እርግጠኛ ነኝ በመጀመሪያ ስለ አለባበሴና ቁመናዬ ማማር ይነግሩሃል፣ ከዚያም በጣም ደረቅ አውኅተኛ ቀጥተኛ ማንንም የማትፈራ ሃቀኛ፣ ለቆመችለት ዓላማ ሟች የሚለውን መልስ እንደምታገኝ አልጠራጠርም። እኒ መላኩ ተፈራ ቶርቸ አስገብተው ቢሞሽልቁኝም ያልተበገርኩ ቆራጥ ነኝ። አሁን እዚህ ሃገር ቢሆንም

ስደተኛውንም ሆነ ዜጋውን ብትጠይቅ ተመሳሳይና የሙብት ተሟጋች የሚለውን ተጨማሪ መልስ እንደምትቀበል አልጠራጠርም። >>

ስላንቺ ቁመናሽ ማማር ለኔ ምን ይረባኛል ብለሽ ነው ስለ ቁመናሽ ማማር የምትገልጭሊኝ? የኢትዮጵያን ሴቶች ቁመና ለማወቅ የሚጓጓው ፈረንጅ ነው እንጂ እንደ እኔው ላላው ኢትዮጵያዊ ስለ የአገሩ ሴት ልጅ ቁመና ማማር እንዴት አዲስ ነገር አድርገሽ ስለ ቁመናሽ ማማር ልትነግሪኝ አንደተገፋፋሽ ግራ ገብቶኛል። ያገሬን ሴቶች ቁመና ማማር አያውቀውም ብለሽ ስላንቺ ቁመና ማማር መግለጽሽ ገርሞኛል። ቁመና ምን ይረባል ብለሽ ነው? ሕሊና ካልተላበሰ ምን ይረባል ብለሽ ነው ስለ የቁመና ማማር መናገር? ኢትዮጵያዊ ሄዋን ቁመናዋ የሚያምር መሆኑን እስከዛሬ ድረስ አያውቅም ይሆናል ብለሽ ከሆነ ፡” አበሻነቴን” የተጠራጠርሺኝ ይመስላል።አይሁድ ነኝ ብለው የእስራል ወታደር ሆነው ጠመንጃ አነግተው በዛው ኑግ በመሰለ አብረቅራቂ ሽጋ መልካቸውና ዘንዶ ወገባቸው አየተራመዱ ሲሄዱ እኮ፡አይቻቸዋለሁ። አዎን ያምራሉ፤ ሌላውን ያስነቃሉ። ታዲያ ያ ውበት እኰ ኢትዮጵያዊ ነው። ያባይ ወንዝ ጠጥቶ ያደገ የወይን ጸጉርና ቁመና ምን ይወጣዋል። ለኔ ያስከፋኝ ቁመናሽ ሳይሆን ሕሊናሽ፤“ኢትዮጵያዊ፤ኤርትራዊ፤ሱዳናዊ፤ ኡጋንዳዊ.....ጥቁር...ስደተኛን” በሌብነት በዘራፊነት የሚወነጅል “ዘረኛ ሕሊናን ይዘሽ እነሱ የሚደግሙትን ዘረኝነት መድገምሽ ነው ከቁመናሽ ጋር አይስማማም የምለው።ስለ ቁመናሽ እና ስለማንነትሽ እንዲነግሩኝ የጠቀስሻቸው ምስክሮች ስም መደርደሩ ለኔ ምን ይረባኛል ብለሽ ነው? እነሱን ከመጠየቅ ቁመናሽ እንዳይልሽ ከፈለግሽ ፎቶግረፍሽን ብትልኪ ምስክርነቴን ልንግረሽ እና ስላንቺ ያለኝን የቁመናሽ ሚዛን በደስታ ልገልጽልሽ እችላለሁ። በተረፈ ከምታንጸናርቂው የስደተኛን ማንኳሰስ ባህሪ ጋር ቁመናሽ አብሮ አይሄድም።

<<እኔ በተፈጠሮዬ ውሸትና ውሸታም ከእናቴ ልጅ

ጋርም አጣልቶኝ ንግግር ተነሳስተናል። እንኳንስ ወሸትን ልናገረውየሚናገረውም ያስጠላኛል። >>

የናትሽ ልጅ ውሽታም ነው ብለሽ መወንጀልሽ አንቺን የአንቺን ሀቀኛነት አላሳየኝም። ምናልባት እሱም በበኩሉ አንቺን በተመሳሳይ እየከሰሰሽ ከሆነስ በምን አውቃለሁ እና ነው አንቺን ሃቀኛ እሱ ውሸታም ብየ አንቺን ‘በሃቀኛ” ልቀበልሽ የምትጥሪው? የናትሽ ልጅ “ውሸታም ነው” ብለሽ ለኔ ቤተሰብ ላልሆንኩ ሰው ስለ ወንድምሽ ምስጢር እና አንቺ ከወንድምሽ ጋር ስላለሽ ሽካራ ግንኙነት መግለጽሽ “እስራላዊነት” የምትይው ባህልሽ አንደሆነ እንጂ “ኢትዮጵያዊነት” ባሕል በኛ ውስጥ ነውር ነው። በጣም ነውርም የነውርም ነውር ነው። ያማረ ቁመና አለኝ ለምትይው ቁመናሽ ጋር አብሮ አይመሳሰልም።

<<የማታውቀውን ሰው ወሸታም ስትል ትንሽም አይከብድህ?>>

ስለቤተሰብ ምስጢር ዓለም ሁሉ ይወቅልኝ ብለሽ ወንድምሽን “ውሸታም” እያልሽ ከወነጀልሺው “አንቺ ድሮ ድሮ አይሮፕላን ላይ ስትወርጂ የዜግነት ወረቀት አይሁዶች ሰጥተውኛል እና ባዲስ አይሁድነት ዜጋዬ “ጥቁር አፍሪካኖችን” ሆስፒታል ዘራፊዎች ናቸው እና “ይባረሩ ፤ይታሰሩ” ብለሽ ለምትይ ሴትዮ ምን ብየ ልጠራሽ ትጠቢቅያለሽ?

<<አኔ ካለባበሴ ጀምሮ እስከባህሪዬ በግብረገብና በሥነ-ሥርዓት ታንጼ ያደኩና ልጆቼንም እንደዚሁ ያሳደኩ፣ በሰው አክባሪታቸው ከሰፈሩና ካካባቢው በነጩም ሆነ በኛው ህብረተሰብ የተመሰገኑና፣ ሁሉም የመጀመሪያ ድግሪ ባለቤቶችና የሁለተኛ ድግሪ ባለቤቶች ሁነው በመያቸው እራሳቸውን፣ ህዝባቸውንና ሃገራቸውን የሚጠቅሙ ግሩም ዜጋዎች፣ በተለይ

ኢትዮጵያዊነትን የተላበሱ ናቸው። >>

ኢትዮጵያዊ መላበሳቸው የምፈልገው እና የማከብረውም የማደንቀውም ጭምር ነው። መማርሽም ድግሪ ማግኘትሽ በጣም እኮራባችኋለሁ። ስላንቺ ብቻ ልናገር። ኢትዮጵያዊነትን የተላበሰኩ ነኝ የምትይ ከሆነ “አፍሪካዊ ስደተኞችን” አገር ያጠፉ፤ወንጀለኞች ዘራፊዎች፡” እያልሽ ከሲናይ በረሃ የተሰቃዩ እና ከባርነት ያመለጡ ስደተኞች እንዲወጡ የዘረኞችን ድጋም መድገምሽ ግን “የተማርሺው” ትምህርት የት እንደጣልሺው ግራ ይገባኛል።ሌላ ቀርቶ በአይሁዶች እንደ ከብት የተከበቡ በባርነት የተያዙ “ፍልስጤማያንን” እንኳ “መብታቸውን” ላለማወቅሽ የምታንጸባርቂው “ድንቁርና” ትምህርትሽ ዋጋ ቢስ አድርጎታል። አንቺ የእስራል ወታደር ሆነሽ ከነበር የያዝሺያቸው ፍልስጤማዊያን በሙሉ “ሽብርተኞች” ናቸው ብለሽ ታምኚያለሽ? በጦርነት ሲያዙ ሆስፒታል አስገብተን አስተምረን ፤”ወፍረው፡ “አምሮባቸው” ነው “ከእሰራኤል እስር ቤት የሚወጡ” ስትይ፡ከተማረ ሕሊና አንደበት የሚወጣ ነው? አስሮ ከብበ አንደከብት “ማወፈሩስ” ይቅር ምናለ ፣መላው ዓለም ያስተላለፈውን ውሳኔ አክብረሽ “አገራቸወን” ብትለቁላቸው እና የግንባታው ስራ አቁማችሁ በሰላም አንድትኖሩ “መሪዎችሽን” ጫና አታደርጊላቸውም? አንቺን እዛ ጦርነት ደምበር እሳት ከሚነደው ደምበር ላይ ወስደው ማስኖራቸውስ ምን ይረባል? አሁን አንቺ እውነት አይሁድ ነኝ እና እየኖርኩበት ያለሁ ቦታ የምትይው “የወላጆችሽ መሬት እና ርስት ጉልት የነበረ ነው ብለሽ ነው እየኖርሽበት ያለው?” ትንሽ ሕሊናሽን ያዝ ማድረግ ምን ይከብድሻል? ትምህርትሽ ይህ ነው?

<<አሁንም ኢትዮጵያን በተመለከተ እንቅስቃሴ ከሚያደርጉት አንዷ ነኝ። ንቁ ተሳታፊም ሌት ተቀን የምቃትት።ኢሳትንም በገንዘብ በልጄ ስም ከሚደግፉት ግንባር ቀደሚነኝ። በልጄ ስም የነበረው ምክንያት ነበረኝ፣ ከ-2013 ጀምሮ ግን በራሴ ስም

ይሆናል>>

ኢሳትን በገንዘብ መደገፍሽ የራሲሽ መብት ስለሆነ አልቃወመውም። ኢሳትን ስለረዳሽ ወይንም ስላልረዳሽ ኢሳት መመዘኛ ፍርድ ቤት አይደለም። በዚህ ጣቢያ ውስጥ ሁሉም ባይሆኑም አራሳቸው ሚዛን ውሰጥ ገብተው መለካት ያለባቸው ከበስተጀርባ ተደብቀው ጣቢያውን የሚያካሂዱት እና ከውስጣቸውም ገብተው የተሰገሰጉ አንዳነድ አሳፋሪ፤አድርባይ፤የባንዳ ስራ እና ፕሮፓጋንዳ ዘመቻ የሚያንጸባርቁ አንዳንድ መናኛ ግለሰዎች አሉባቸው። እንዳንቺው ያለው ግብዝ ደግሞ "እንደነሱ ያሉት" የፍየል ዓይን የዋጡ "ድብልቅልቆች" ለማወቅ ያስቸግርሻል። እኔ የምቃወመውና ያልወደድኩልሽ ነገር "አማራን የመጥላትና የዘረኝነት ባህሪሽን ብቻ ነው፡" አማራዎች እንዲህ አደረጉን" የምትይውን ነው እኮ "ውሽታም ነሽ ያልኩሽ" እንጂ ኢሳት ረዳሽ አልረዳሽ ጉደዩ አይደለም። ለመሆኑ "አማራውን በጠላትንት ስለፈረጅሺው 'አማራውን' በፕሮግራማችሁ አመናኘኩልኝ" ለማት ነው ኢሳትን በገንዘብ የምትረጂው? እኔ የምጠይቅሽ፤አማራው እና አንቺ በምን መንገድ ነው የተጣላችሁት? እኔን አማራ ነህ ብለሺኛል፡ ወላጆቼንም አማራ ናቸው ብለሻቸዋል። እነዚህ አማራ ናቸው የምትያቸው ቤተሰቦቼ አንቺን እና ወላጆቺሽንን በምን፤በምን ሁኔታ በደልናችሁ? ወላጆቺሽንስ በምን እና እንዴትስ የትስ ተገናኝተው ነው ያንቺን "አይሀዳዊ ቤተሰቦችን" ጨቁናችሗቸዋል ብለሽ እኔም ወላጆቼንም የምትወነጅልን? ወላጆቼን የት ነው ወላጆቺሽን ሲጨቁኗቸው ወይንም ሲሰድቧቸው የሰማሺው/ያየሺው? ወላጆቺሽ ስለ ወላጆቼ ታሪክ እና ማንነታቸውስ ምን ብለው ነገሩሽ ? ውሽታም ያልኩሽ እኮ እንዲህ ያለውን ዓይን ያወጣ የማይገናኝ ውሽት "ስትዋሺ" እያነበብኩሽ ነው። "አትዋሺ" የምልሽ። ዲግሪ አለኝ፤"ሰብአዊ መብት ተሚጋች ነኝ" የምትይው ትምህርት ወላጆቼ እና ወላጆቺሽ ጋር በምን በምን አያይዞ ይህንን ውሸት እንድትዋሺ እንደገፋፋሽ በጣም እንቆቁልሽ ነው?

<<ምንም ቢሆን አያት ቅድመ አያቶቼ ለ-2500 ዘመን

ሲኖሩባት በጀግንነት የተሰወባት ሃገር ናት። አጥንታቸውም እዚያው ተቀብሮ ቀርቷል። ምንም እንኳ አንተና ቤተሰቦችህ የተጠናዎታችሁ ሁዋላ ቀር ባህል አለቃችሁ ብሎ፣ አጽማቸውን እየፈነቀላችሁ መድሃኒት እያላችሁ አንገታችሁ እንደምታስሩት ብናወቅም፣ አጽማቸው ያረፈበትን ለም መሬት እየፈነቀላችሁ በማረስ እህል እያበቀላችሁበት መሆኑን ብንረዳም፣ አንድ ቀን ጥሩ አስተዳደር ሲሰፍን መልሱን ትሰጡናላችሁ ብዬ አምናለሁ። ያም ሆነ ይህ ግን አንተ አገር ወዳድነትህ ድህረ-ገጽ ላይ ስለቀለቅህ አይደለም። 'የአህያ እቃው በሆዱ" ይባል የለ። አንተ አይደለህም ምስክርነት የምትሰጠኝ።
ክርስቶስ እኮ ከአንተ ይልቅ ይሁዲዎች ያወቁታል፣ ወንድማቸውም ነው። በሃይማኖትም ሆነ በዘር ከይሁዲዎቹ ምርያምና ዮሴፍ በመወለዱና እድሜው ሰላሳ ዓመት እሰኪሆነ ውድረስ እኮ በአባቱና በእናቱ እምነትና ሃይማኖት የኖረ ነው። ከዚህ በሁዋላ የ ማፈልገውን እምነት መከተሉ ማንም አይከለከለውም። ከሰው መወለዱን ግን የአንተ ሃይማኖት መሪዎችም አይክዱትም። የተሰሩትን ፊልሞች አይቻለሁ፣ መጽሃፉን አንብቤዋለሁ። አለማመን የ ሙብት ጉዳይ ነው። >>

የናንተን ሞተ ሰው አጽም እያሸተትን ወደ ኋላ የቀረን መሆናችን ስትሰድቢኝ፤ ከመገረም ሌላ ምን እላለሁ ብለሽ ነው? ሌላ ቀርቶ ስለ ክርስቶስ አይሁድ ሆኖ እንደገና አይሁድ ሃይማኖት ተከትሎ እንደገና ሃይማኖቱን ለውጦ ወደ ሌላ መለወጡ አይሁዳዊዋ አንቺ የምታውቂውን “ዘመዴ/ወገኔ የምትይውን ክርስቶስን” ትምህርት ልታስተምሪኝ መመኮርሽም ስለ የቅርብ ዘመድሽ እየሱስ እውቀትሽ

አስተምህሮ አመሰግናለሁ። ሰለ ክርስቶስ በበለጠ ዘመዴ ነው የምትይውን ከክረስቶስ ጋር ያለሽን የስጋ ዝምድናሽ የደም ቆጠራሽ መብትሽ ነው። ዋናው ነገር አይሁዶች "ሃይማኖቱ ለውጧል" ብለው ነው "ይሰቀል፤ይሰቀል" ያሉት ወይስ ከዚያ በላይ ያለማራቸው ትምህርት ስለነበረ ነው? በአይሁድነትሽ ክርስቶስ ዘመድሽ ከሆነ የምታውቂው ያስተማሩሽን ይሄ ከሆነ ዘርዘር አድርገሽ ብታስተምሪኝ አመሰግናለሁ? መቸም ሃይማኖቱ ስለለወጠ ነው የሚል ትምህርት ያገኘሁት ለመጀመሪያ የሰማሁት ከክረስቶስ ዘመድ ከአይሁድ አፍ መስማቴ ለመጀመሪያ ነውና እየሱስ በኋላ አይሁዳዊ ሃይማኖት ከድቶ ወደ ሌላ ተለወጠ የምትይው "የሃይማኖት ስም" ምን ነበር "አርቶዶክስ"? ወይ ጉድ! ይሄ "ዲግሪ" የሚባል መአረግ ስንቱን አሳብዷል? ለመሆኑ አንቺ እንደ አይሁድነትሽ አንቺ እና ክረስቶስ "ዝምድናችሁ ምን እና ምንድነው"? ወላጆችሽ አልነገሩሽም? የኔ እህት? (የኔ እህት ስልሽ ወንደሜ አይደለህም ብቻ እንዳትይኝ እንጂ) የክረስቶስ የስጋ ዘመድ ጋር "እህቴ' ነሽ ብሎ አንድ ሰው ቢሸቀዳደም "አንደማትኩራሪ" ተስፋ አለኝ። እኛን ለማግባት ይሽቀዳደማሉ የምትይው መኩራራት ጋር እንደታያይዢው ብየ ነው። የክርስቶስ የስጋ ዘመድ "እህቴ" ብሎ ማለት እሽቅድድም ቢገባም "አያስከፋም" ብዬ ነው።

<<በል በቃኝ። እኔ ግን አንድ ቀን ወደዚህች ቅድስት ሃገር ለመምጣትና በዚህም አድርገህ ቤተ-ልሄምና ራማላ ፍልስጤሞቹ ጋር መሄድ ከፈለክም በኢትዮጵያዊነቴ በሚገባ አስተናግድሃለሁ። በመኪናም ያለምንም ወጭ እገዛ ለማድረግ ቃል እገባልሃለሁ። ማየት ማመን ነውና!>>

ፍልስጢኤሞች እኮ ከኔው ይልቅ ላንቺው ለአይሁድ ዘመዶቺሽ ናቸው የሚቀርቡት። የይስሃቅ እና የእስማኤል፤ቤተሰቦች ናችሁ ነው እኮ የሚባለው? ለነሱ ለዘመዶቺሽ ያልሆንሽ ለዚህ ጥቁር አፍሪቃዊ

ማስተናገድሽ እንዴት ቀለለሽ? በአማራነቴ እና “አማራዎቹ” ወላጆቼ “አይሁዶቹን” ወላጆቺሽን መበደላቸው በዝርዝር ሳትገልጪሊኝ? ከዚያስ በፍልስጢሞች እና በናንተው ባንቺው አይሁደዊቷ መካካል ያለው ጥላቻ፤ ቂም፤እልህ፤ጀብደኝነት፤ዘረኝነት፤ሽብር፤ መገዳደል፤ያለ መሬትህን መያዝ፤መስፋፋት፤መሰዳደብ....ያለውን ችግር መፍትሔ “መጀመሪያ ሳታስተናግጂ” እኔኑን ጨቁነሸኛል፤የምትይኝን የሩቁው “አማራን” ማስተገድሽ እንዴት ሊቀልሽ ነው? ለማንኛውም እኔም እኮ “ከቅድስት ከተማ” ከኢትዮጵያዊት ቅድሰት መሬት ላይ መወለዴ የረሳሺው መሰለኝ። የምር አይደለም እንጂ መስተንግዶሽ የምር ከሆነ በአክብሮት እቀበላለሁ። ስላከበርሺኝ እኔም አጠፋውንም ለመመለስ “ቅድሰት መሬት አክሱምን” እንድተሳለሚ እና ሓውልቶቿንም እንድትጐበኚ “ወደ ሕሊናሽ” እንድትመልሺሽ ትረዳሽ ዘንድ “ቅብአተ ሜሮኑዋን፤ፀበሏንም” (አይሁድ ነኝ ብለሽ ካልተጠየፍሺው) እንድትጐበኚና እንደትቀቢው እርዳታውን አደርግልሻለሁ።ያ የሚሆነው ግን “አገሬን እያዋረዳት ያለው እንዳንቺው ‘አማራን፡ የሚጠላ’ ወያኔ የተባለ አርኩስ ሲወገድ መሆኑን ግንዛቤ አስገቢሊኝ። በተረፈ እኔን ለማነጋገር እና እዚህ ጉዳይ ግልጽ ያልሆነልሽ ነገር ካለ ምን ጊዜም ላብራራለሽ ዝግጁ ነኝ። ስልኬም፤ ኢመይሌም አግኝተሺዋል። በነገራችን ላይ “የድሮው የአክሱም ማርያም ቤተክረስትያን ውስጥ ሴት ገብታ ማስቀደስ የተከለከለ” ነው። ቀር እንዳይልሽ። አይሁዶች ብቻ አይደሉም የተወሰነ መብት ያጡት፤ ሴቶች ክረስትያኖች/ትግሬዎችም ወደ እዛው መቅደስ መግባት ክልክል ነው። አየሽ ሁሉም የየራሱ እሮሮ አለው። አክሱም እስላሞቹም ይህንን እያወቁ እነሱ ብቻ ተጠቂዎች አድርገው የሚመለከቱበት እሮሮ አስፍተው ይመልከቱ እያለኩ ለእላም ተሟጓቾች ወንድሞች እና እህቶች ሁሌም የምሞግታቸው እና የምምክራቸው ለዚህ ነው።ልዩ ተጠቂ ነኝ ማለቱን አቁሙ ብዬ ሁሌም የምጮኸው ይኼንኑ ነው። ሂሊናችሁ ይስራ።

ውድ ወ/ሮ ሃና መከተ፡

በመጨረሻ ያንቺን እንግዶትንት ለመቀበል ከፈለግሽ “ይህንን

የአይሁዶቹን በጥቁር ስደተኞች ላይ የሚሰነዝሩት የጥላቻ “ዘረኝነት” ከጥቁሮቹ ጋር ወግነሽ “ዘረኝነትን” ካልተቋቋምሽ፤ እንድጐበኚ የምትጋብዢኝን ጥሪ አልቀበለውም። ያንን ስታደርጊ ነው “ያንቺን መስተንግዶ” ልባዊ የማደርገው። ይህን ሳታይ አንዳትቀሪ አደራ።

**Racism vs. Africans in Israel (1/4)**

**http://youtu.be/rYwvGHY1nAI**

በተረፈ ጽሑፍሽን በትዕግሰት እንዳነበብኩልሽ በትዕግሰት እንደምታነቢኝ ተስፋ አለኝ። በጣም ነው ያስቆጣሺኝ። አንቺ እህቴ እኔ ደግሞ የስጋ ወንድምሽ መሆንን ግን ለደቂቃም እንዳትጠራጠሪ።፡ ሰላምና ጤና ላንቺ እና ለቤሰቦችሽ እንዲሆን ኢትዮጵያዊ ምኞቴ እና ተስፋዬ ነው። ጌታቸው ረዳ ከአሜሪካ አገር። getachre@aol.com

www.ethiopiansemay.blogspot.com

(408) 561-4836